በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐ
Solomon Yoha
271607

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐ
Solomon Yoha

# ድንግልናዊ ፡

## ሕይወት ።



«ስለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡
ብቻ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ጃንደ
ረባ ፡ ያደረጉ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። ማስ
ተዋል ፡ የሚችል ፡ ግን ፡ ያስ
ተውል» (ማቴ ፡ ፲፱ ። ፲፪) ፡

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡
ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በነገሡ ፡ በ፴፩ኛው ፡ ዓመት ፡
፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ተጻፈ ።

www.ethiopianorthodox.org

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
D.N Solomon Yo…

# ድንግልናዊ ፡

## ሕይወት ።



ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
09118601…
0111/2716…
D.N Solomon Yohannes

«ስለ ፣ መንግሥተ፣ ሰማያት ፣
ብቻ ፣ ሰውነታቸውን ፣ ጃንደ
ረባ፣ያደረጉ፣ ሰዎች፣አሉ። ማስ
ተዋል ፣ የሚችል ፣ ግን ፣ ያስ
ተውል» (ማቴ ፣ ፲፱ ፡ ፲፪) ፣

ይህ ፡ መጽሐፍ ፣ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡
ኃይለ ፣ ሥላሴ ፣ በነገሡ ፣ በ፳፬ኛው ፣ ዓመት፣
በ፲፱፻፵፮ ፣ ዓ. ም. ተጻፈ ።

www.ethiopianorthodox.org

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
D.N Solomon Yohannes
0911860113
0111/271609



የጠፋውን ፡ የሚመልስ ፡ ያረጀውን ፡ የሚያድስ ፡
ታላቁ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።

www.ethiopianorthodox.org

የዚህ ፣ መጽሐፍ፣ መታሰቢያነቱ ፣ ስለ ፣ እግዚአብሔር ፣ መንግሥት ፣ ስፋት ፣ እንዲሁም ፣ ወገንን ፣ ለመርዳት ፣ ዕውቀትን ፣ ለማዳረስ ፣ ዘመናቸውን ፣ ሁሉ ፣ በንጽሕና ፣ በድንግልና ፣ ለሚያሳልፉ ፣ ተሰጠ ።

በሙሉም ፡ ሆነ ፡ በከፊል፡
ማሳተሙ ፡ የደራሲው ፡
መብት ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ው ጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩. | መቅድም ፡ ... ... ... ... ... | ፯-፲፩ |
| ፪. | የድንግልናዊ፡ ሕይወት፡ ፍች ፡ ... ... .. | ፲፩-፲፭ |
| ፫. | » » ዓላማው ፡ ... ... ... | ፲፭-፳፬ |
| ፬. | » » ጥቅሙ ፡ ... ... ... .. | ፳፬-፴፬ |
| ፭. | ድንግልናዊ፡ሕይወት፡መቼ፡ተጀመረ፤ ... .. | ፴፬-፵፪ |
| ፮. | ወንድማማችነት ፡ . ... ... ... ... ... | ፵፪-፶ |
| ፯. | የድንግልና ፡ ጊዜ ፡ ... ... ... ... ... | ፶-፷፪ |
| ፰. | የምንኵስና ፡ ሕይወት ፡ ... ... ... ... | ፷፪-፸፯ |
| ፱. | ማጠቃለያ ፡ ... ... ... ... ... | ፸፯-፹፱ |


## መ ቅ ድ ም ።

የድንግልና ፡ ሕይወት ፡ ከጥንት፡ ከአባቶች ፡ ጀምሮ፡ የተከበረ ፡ በማንኛውም ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነበር ፤ ይኸም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ የጥንት ፡ ሕዝቦች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ዘዴና ፡ ጥናት ፡ አድርገውለት ፡ ሲሠሩበት ፡ ቈይቷል ፤ ማለት ፤ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ዕድሜው ፡ ወይም ፡ ችሎታ ውና ፡ ስሜቱ ፤ የኑሮውም ፡ ደረጃ ፡ ማግባት፥ እስከ፡ ፈቀደ ለት፡ ዘመን፡ ድረስ ፡ በድንግልና ፡ መኖር፡ ግዴታው፥ ስለ፡ ነበር ፡ የሴቱና ፡ የወንዱ ፡ ነገድ ፡ እንዳይገናኙ ፡ እንዳይተ ያዩ ፡ ወይም ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ ስሕተት ፡ እንዳይሠሩ ፡ በማለት ፡ በልዩ ፡ ዘዴ ፡ ይጠበቁ ፡ ነበር ፡ በተለይም ፡ በእ ስራኤል ፡ ዘንድ ፡ እንኳ ፡ ድንግልናን ፡ ማጥፋት ፡ በልዩ ፡ ልዩ፡ አኳኋን፡ የጋብቻን፡ ዓላማ፡ የሚያጠፋትን፤ ዝሙትም፡ የሚሠሩትን፡ የሚቈጣጠር፡ ከባድ፡ ሕግ፡ነበራቸው ፤ማለት፡ በሕግ፡ ካገባው፡ ሰው፡ በቀር፡ ሕግን፡የተላለፈውን፡በእሳት፡ አቃጥለው ፤ በድንጋይ ፡ ወግረው ፡ ይገሉት ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ ንጽሕና ፡ ድንግልና ፡ በጣም ፡ ተጠብቆ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፤ ማለት ፡ በነርሱ ፡ ዘንድ ፡ በቀላሉ ፡ ተጋብቶ ፡ በቀላሉ ፡ መፋታት ፡ ስለሌለ ፡ ወንዱም ፡ ሁነኛውን ፡ እስኪያገኝ ፡ ሴቷም ፡ የሚሆናትን ፡ እስክታገኝ ፡ ድረስ ፡ በድንግልና ፡ መኖር፡ ግዴታቸው ፡ ነበር። በዚህም፥ ምክንያት፥ የዕድሜ፥ ልክ ፡ ድንግልና ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ታሪክ ፡ ይነግረናል ።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ የድንግልና ፡ ሕይወት ፡ ከፍተኛውን ፡ ደረጃ ፡ ይዞ ፡ ይኖር ፡ ነበር። ድንግል፡ ማለትም ፡ ለወንዱም ፡ ለሴቱም ፡ የክብር ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ይገኝ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ይመሰክራል።

ወደ ፡ ጥንታዊው ፡ ግሪክ ፡ ዐይነ ፡ ልቡናችንን ፡ የመለስን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ደናግል ፡ ተለይተው ፡ የሚኖሩበት ፡ በዕውቀት ፤ በሥልጣኔ ፡ ይገለምሱበት ፡ የነበረ ፡ ቦታ፡ ተለይቶ ፡ ፓርቴናጐግዮን፡ የሚል፡ ስያሜ፡ እንደ፡ ነበረው፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ያሉት ፡ የግንቦቹ ፡ ፍራሽ ፡ ያስረዳሉ ።

በኛ ፡ በሀገራችንም ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ልጆች ፡ የተባሉት ፡ ሴቶች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ በሞግዚቶች ፤ በወላጆች ፡ እየተጠበቁ ፡ በክብር ፤ በማዕርግ ፡ ያድጉ ፡ እንደ ፡ ነበር ፤ ወንዶች ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ገዳም ፡ እንደ ፡ አምባ ፡ ያለ ፡ ከሰው ፡ የተለየ፡ ቦታ ፡ ተሰጥቷቸው፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡ ያድጉ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ ያስረዳናል ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ቦታዎቹም ፡ ይመሰክራሉ ።

በዝቅተኛውም ፡ ሕዝብ ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ሁሉ ፡ ሳይዘገዩ ፡ በፍጥነት ፡ ስለሚጋቡ ፤ እስከዚያው ፡ የተቻላቸውን ፡ ጥበቃ ፡ ሳያደርጉ ፡ አይቀሩም፡ ነበር ፡ ግን፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ሳያደርሱ ፡ ክፉውንና ፡ ደጉን ፤ ጠቃሚውንና ፡ ጐጅውን፡ ሳያውቁ ፡ በወላጆቻቸው ፡ እየተነዱ፡ አግ



ብተው ፡ ለኑሮ ፡ ዕንቅፋት ፡ የሆኑ ፡ አይጠፉም ፡ ምክንያቱም ፡ ስሜቱ ፡ ትዳር ፡ ለመያዝ ፡ የማያበቃው፡ መሆኑን ፡ ሲያውቅ ፡ እንቢ ፡ ሊል፡ ስለማይችል ፡ እንዲሁ ፡ ተገድዶ ፡ አግብቶ ፡ የሁለት ፡ ዓለም ፡ ስደተኛ ፡ ሁኖ ፡ ሲንቀዋለል ፡ ይገኛልና። ይኸ ፡ ሰው፡ በድንግልናው ፡ ተጠቅሞ ፡ ሰውን፡ ይጠቅም ፡ ኑሮ ፡ እንደሆን ፡ ሳይታወቅ ፡ ተሰነካክሎ፡ ለመኖር ፡ ጋብቻው ፡ ምክንያት ፡ ሆነው ።

በአሁኑ፡ ጊዜ ፡ በዕድሜ፤ በዕውቀት፡ እስኪጐለምሱ፡ የጋብቻው ፡ ኑሮ፡ መቈየቱ፡ መልካም፡ ሲሆን ፤ ስለ፡ ንጽሕናቸው፡ጥበቃ፡ ደግሞ፡ ምንም፡ የተወሰደ፡ እርምጃ፡ ስለሌለ፤ የድንግልና ፡ ሕይወት፡ እየቀለለ ፤ ዋጋም ፡ እያጣ ፡ መሄዱ፤ የማይጠረጠር ፡ ነው ። ስድ ፡ የለመደውም ፡ ሰው ፡ በኋላ ፡ ትዳር ፡ ሊይዝ ፡ በአንድም ፡ ሊጸና ፡ አይችልም ፡ ይኸም ፡ ከሆነ ፡ ወጣቱ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ገና ፡ ከመምጣቱ ፡ ፈተና ፡ ሲከተለው ፡ ችግሩ ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለሀገርም ፡ ሁሉ ፡ ይሆናል ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ለማንኛውም ፡ እንግዳ ፡ ለሆነበት ፡ ነገር ፡ የግድ ፡ መሪ፡ ያስፈልገዋል። የመጀመሪያ ፡ ስሜቱ ፡ እንደመሪው ፡ አገላለጥና ፡ አስተያየት ፡ ነው ፡ የወጣትም ፡ ስሜት ፡ እንደ ፡ አሳዳጊውና ፡ እንደ ፡ ጠባቂው ፡ ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

አንድ ፡ ወጣት ፡ ለማናቸውም ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ ጐጅነቱን ፡ ዐውቆ ፡ እስኪተወው ፡ ጠቃሚነቱንም ፡ ዐውቆ ፡ እስኪሠራው ፡ የግድ ፡ ጥበቃና ፡ አመራር ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ።

የማንኛውም፡ እርምጃ ፡ እንደ ፡ አስተዳደጉና፡ እንደ፡ ልምዱ ፡ ነው ፡ እንኳን ፡ በአርአያ፡ ሥላሴ ፡ የተፈጠረው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፤ እንስሳት ፡ አራዊት ፡ ቢሆኑ ፡ እንደ ፡ አስተዳደጋቸው ፡ እንደ ፡ ልምዳቸው ፡ ሲራመዱ ፡ እንደሚገኙ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዞአሎጅ ፡ የሚገኙት ፡ እንስሳት ፡ አስረጅ ፡ ይሆናሉ ።

ስለዚህ፡ ለወላጆችና፡ ለልዩ፡ ልዩ ፡ ድርጅቶች ፡ መምሪያ፡ ትሆን ፡ ዘንድ፡ ይህችን ፡ ጽሑፍ፡ ሳበረክት፤ ሁላችን ፡ የንጽሕናን ፡ የድንግልናን ፡ ጠቃሚነት ፡ በመረዳት ፡ እንሠራ ፡ ዘንድ ፡ ከማሳሰብ ፡ ጋራ ፡ ነው ።

ሊቀ ፡ ሥልጣናት ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ወርቅነህ ።

# ክፍል ፡ ፩ ።

## ድንግልናዊ ፡ ሕይወት ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የቃሉ ፡ ፍች ።

ድንግል ፡ ማለት ፡ ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ ምንም፡ ያልተቀላቀለበት ፡ ምንም ፡ ያልተሠራበት ፡ እንዲሁ ፡ በተፈጥሮው ፡ ያለ ፡ ማለት ፡ ነው ። የቃሉን ፡ እውነተኛ ፡ ፍች ፡ ለማግኘት ፡ ስንፈልግ ፡ ግን ፤ ለየነገሩ ፡ ሰጥቶ ፡ መተርጐም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ እንረዳለን ፡ ስለዚህ ፡ ለዕቃ ፡ የሰጠን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ድንግል ፡ ማለት ፡ ምንም ፡ ያልተሠራበት ፡ ገና ፡ ከፋብሪካው ፡ የወጣ ፡ ያላደፈ፤ ያልጐደፈ፡ ያላረጀ ፤ ያላፈጀ ፡ ማለት ፡ ይሆናል ፡ ለመሬት ፡ የሰጠን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ድንግል ፡ ማለት ፡ ያልታረሰ ፤ ያልተቈፈረ ፤ ዘር ፡ ያላረፈበት ፤ እንዲሁ ፡ በተፈጥሮው ፡ ያለ ፡ ማለት ፡ ይሆናል። በዚህም ፡ አኳኋን፡ ለሰው ፡ የሰጠን ፡ እንደ፡ ሆነ፤ ድንግል ፡ ማለት ፡ የተፈጥሮ ፡ ንጽሕናውን ፡ የጠበቀ ፡ ንጽሐ ፡ ጠባዩ ፡ ያላደፈበት፡ እንደ፡ መላእክት፡ በንጽሕና ፡ የሚኖር ፡ ወንድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሴት ፡ የራቀ ፤ ንጽሕ ፡ የጠበቀ፤ ሴት ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ ከወንድ ፡ የራቀች፡ ንጽሕናዋን ፡ የጠበቀች ፡ ማለት ፡ ነው ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የቃሉ ፡ ፍች ፡ ሊውል ፡ በዐረፍተ ፡ ነገርም ፡ ሊገባ ፡ የሚችለው ፡ በመጨረሻው ፡ አስተያየት ፡ ነው ። በድንግ

www.ethiopianorthodox.org

ልና ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች፡ የመላእክትን ፡ ዓለም ፡ ይወርሳሉ፤
የመላእክትን ፡ ሕይወት ፡ ገንዘብ ፡ ያደርጋሉ ፤ ግን ፡ ለማ
ንኛውም ፡ ሰው ፡ ድንግል ፡ የሚያሰኘው ፡ መጥፎውን ፡
ነገር ፡ ከመሥራት ፡ ብቻ ፡ መራቅ ፡ ሳይሆን ፡ ከማሰብም ፡
ከመናገርም ፡ ከማየትም ፡ እንዲሁ ፡ ድንግል ፡ የሆነ ፡ እን
ደሆነ ፡ ነው ። ድንግል ፡ ማርያም ፡ በነፍስም ፡ በሥጋም ፡
ድንግል ፡ ስለ ፡ ሆነች ፤ ድንግል ፡ በ፪ኤ ፡ ትባላለች ። የድ
ንግልናን፡ ጠቃሚነት ፡ ስንናገር ፡ ጋብቻን ፡ መንቀፋችን፡
ስለ ፡ ጋብቻም ፡ ስንናገር ፡ ድንግልናን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ማድ
ረጋችን ፡ አለመሆኑን ፡ በ፪ቱም ፡ ማዕርግ ፡ ያለ ፡ ይረዳው
ዘንድ ፡ ይገባል ። ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሁለቱም ፡ ዐይነት፡ ሕይ
ወት ፡ ተስማሚና ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ እያንዳንዱ ፡
ሰው ፡ እንደ፡ ምርጫው ፡ እንደ ፡ ጀመረው ፡ እንዲፈጽም፤
ያለበትንም ፡ አክብሮ ፡ እንዲይዝ ፤ በምርጫውም ፡ ታላቅ
ጥንቃቄ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ። ክርስቶስ ፡ ሁሉም ፡ በየተ
ሰጠው ፡ በየጀመረው ፡ መፈጸም ፡ እንዲገባው ፡ ሲያስ
ረዳ ፡ «ማስተዋል ፡ የሚችል፡ ግን ፡ ያስተውል» ፡ ብሏል ።
(ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪) ፤ ይኸም ፡ ማለት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በድንግ
ልና ፡ በንጽሕና ፡ ቈይቶ ፡ ራሱን ፡ ይመርምር፤ ያስተውል፤
ከዚያ፡ በኋላ፡ በጀመረው ፡ ይፈጽም፡ ማለት፡ ነው። ይኸም፡
አስተያየት ፡ ድንግል ፡ ሁኖ ፡ ቆይቶ ፡ ከድንግልናው ፡
በኋላ ፡ ቢያገባ ፡ ጋብቻውን ፡ አክብሮ፡ በሕጉ ፡ ጸንቶ፡ የጀ



መረውን ፡ እንዲፈጽም ፡ በድንግልናም ፡ ቢኖር ፡ ዘለዓለ
ማዊ ፡ ድንግልናን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጎ ፡ በዚያው ፡ በጀመ
ረው፡ ጸንቶ፡ ድንግልናውን፡ አክብሮ፡ እንዲኖር፡ ያስረዳል።

እንግዲህ ፡ ድንግል ፡ ማለት ፡ ከሴት ፡ ያልደረሰው ፡
ወንድ ፡ ወይም ፡ ከወንድ ፡ ያልደረሰችው ፡ ሴት ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ በግልጥ ፡ ታወቀ ፡ ተረዳ ። የንጽሕና ፡ ጠባያቸው፡
ያላደፈባቸው ፡ በድንግልናቸው ፡ ወዝ ፡ ተቀብተው ፡ በድ
ንግልናቸው ፡ ጌጣጌጥ ፡ አጊጠው ፡ የሚታዩት ፡ ደናግል ፡
ተብለው ፡ ይጠራሉ ፡ ይኸም ፡ ማዕርግ ፡ ይሰጣቸዋል ።
ይኸም ፡ ሕይወት ፡ ከፍተኛ ፡ ሕይወት ፡ ከፍተኛም ፡ ማዕ
ርግ ፡ ነው ። ይኸም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ የሚያልፍበት
ትልቅ ፡ ጐዳና ፡ ትልቅም ፡ ድልድይ ፡ ነው ፡ ማለት፤ ማን
ኛውም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ እስኪያገባ ፡ ድረስ ፡ በድንግልና ፡
መኖር ፡ ግዴታ ፡ እንዳለበት ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባዩ ፡ በትክ
ክል ፡ ይመሰክራልና ። የዓለም ፡ ሊቃውንትም ፡ ይኸንን ፡
በመደገፍ ፡ የወጣቶች ፡ ጊዜ ፡ በንጽሕና ፡ እንዲጠበቅ ፡
በንጽሕና ፡ ሁነው ፡ ጊዜያቸውን ፡ እንዲያሳልፉ ፡ የተለየ፡
ትምህርት ፡ ሲሰጡ ፡ በተለየ ፡ ቦታ ፡ ሲያስተምሩ ፤ የተለየ
ጥንቃቄም ፡ ሲያደርጉ ፡ ይገኛሉ ።

ም ክ ር ።

አንባቢ ፡ ሆይ ፤ አንተ ፡ ወጣት ፡ እንደ ፡ ሆንክ ፡ ድን
ግልናህን ፡ ጠብቅ ፤ የድንግልናህን ፡ ጊዜ ፡ አክብር ፤ ብዙ

www.ethiopianorthodox.org

ዋጋ ፡ ታገኝበታለህ ። የልጅ፡ አባት ፡ እንደ ፡ ሆንክ ፡ ግን፡
ልጆችህ ፡ በዚህ ፡ ጐዳና ፡ እንዲራመዱ ፡ ምክር ፡ አስተ
ምር ። ንጽሕና ፡ ድንግልና ፡ ከብዙ ፡ ቅባት ፡ የበለጠ ፡ ለሰ
ውነት ፡ ጥራትን፡ ለዐይን ፡ ደም፡ ግባትን፡ የሚሰጥ፡ ነው ።
ንጽሕና ፡ ድንግልና ፡ ለጤንነት ፡ ከታወቁት ፡ መድኀኒ
ቶች ፡ ፩ኛውና ፡ የበለጠ ፡ ፍቱን ፡ መድኀኒት ፡ ነው ። ንጽ
ሕና ፡ ድንግልና ፡ ለኀይል ፡ በበለጠ ፡ ብርታትን፡ የሚሰጥ፡
ነው ። ድንግልና ፡ ሁሉን ፡ አርቆ ፡ የሚያሳይ ፡ ከፍተኛ ፡
ቦታ ፡ ነው ። የኑሮ ፡ ደረጃቸውን ፡ በዚህ ፡ ሁነው ፡ ተመል
ክተው፡ ያገቡ ፡ ሁሉ፡ አይጸጸቱም ፡ አያዝኑም፡ ካገቡ፡ አይ
ፈቱም ፡ ከመነኰሱ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ አይመለሱም ። ስለ
ዚህ ፡ ንጽሕናህን ፡ ድንግልናህን ፡ እንደ ፡ ዋዛ ፡ ዕቃ ፡ በከ
ንቱ ፡ አታጥፋው ። ከፍ ፡ ያለ ፡ ፍች ፡ ከፍ ፡ ያለ፡ ግምትም፡
ስጠው ። ብዙዎች ፡ አንተን ፡ የሚያጠምዱበት ፡ ምክን
ያት ፡ ድንግል ፡ ስለ ፡ ሆንክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕወቅ ፤ ከተሰነ
ካከልክ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ ፈላጊ ፡ የለ
ህም ፡ እንደ ፡ ሰባራ ፡ ዕቃ ፡ ትሆናለህ ፤ ማንኛውም ፡ አያ
ምንህም ፤ ታማኝነትህ ፡ ይጐድላል ፤ ይሉኝታህ ፡ ይጠ
ፋል ፤ መጥፎ ፡ ግምት ፡ ይጣልብሃል ። ድንግልና ፡ ለዚ
ህም ፡ ዓለም፡ ለወዲያኛውም ፡ ዓለም ፡ የሚስማማ ፡ ሕይ
ወት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ተጠቀምበት ፤ ድንግልና ፡ የነ
ገሩ ፡ ሁሉ ፡ ማመዛዘኛና ፡ ማጣሪያ ፡ ነው ። ስለዚህ



ሕይወትህን ፡ በዚህ ፡ ሚዛን ፡ ለካው ፤ ገምተው። በድንግ
ልና፡ ሕይወትህ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገልግል
በት ፤ በጎ ፡ አድራጎትን ፡ ፈጽምበት ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

## የድንግልናዊ ፡ ሕይወት ፡ ዓላማ ።

ድንግልና ፡ ከፍ፡ ያለ ፡ ዋጋን ፡ የሚያሰጥ ፡ ሕይወት፡ ነው ፡ ማለት ፡ ለማነኛውም ፡ ሰው ፡ ከባሕርይ ፡ እንስሳዊት ፡ ወጥቶ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋውን ፡ ገቶ ፡ የመላእክትን ፡ ዓለም ፡ ወርሶ ፡ መኖር ፡ ታላቅ ፡ ምርጫና ፡ ከፍተኛም ፡ ዕድል ፡ ነውና ። ዋና ፡ ዓላማው ፡ ግን ፡ ፩ኛ፤ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ የማይለያይ ፡ ግንኙነትን ፡ ለማትረፍ ፡ ነው ፡ ይኸ ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ የሚያገባው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይርቃል ፡ ወይም ፡ ይለያል ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ድንግሉ ፡ ወይም ፡ ያላገባው ፡ በጧት፡ በማታ ፡ በጸሎት ፡ በስእለት ፡ በአስተብቊዖት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይለምነዋል፤ በጸሎት፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይገናኛል ፡ ይነጋገራል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ያገባው ፡ ግን ፡ ሚስቱን ፡ የሚያስደስትበትን ፡ ቤቱ ፡ የሚደረጅበትን ፡ ቀን ፡ ከሌት ፡ ይሠራልና ፡ ማለት ፡ ወጥቼ ፡ ወርጄ ፡ ነግጄ ፡ አትርፌ ፡ አርሼ ፡ ቈፍሬ ፡ ብዙ ፡ ገቢ ፡ ካላገኘሁ ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ አግብቼ፡ እንዴት ፡ አኖራታለሁ፡ ይላል ። ሴቷም ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ አግብቼ ፡ ፈትዬ ፡ ካላለበ

www.ethiopianorthodox.org

ስኵት ፡ ሰፍቼ ፡ ካልሰቀልኩለት ፡ ጠምቄ ፡ ካላጠጣሁት ፡
ጋግሬ ፡ ካላበላሁት ፡ እንዴት ፡ ይኖርልኛል ፤ የፍቅር ፡
መግለጫውስ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ በጧት ፡ በማታ
አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ሲያስቡ፡ የእግዚአብሔር፡ ፈቃድ ፡ ይጐድ
ልባቸዋል ። ይኸም ፡ ሊሠራ ፡ የሚገባ ፡ ቅዱስ ፡ ተግባር ፡
ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በበለጠ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ስለሚያደላ፡ፈጣ
ሪውን ፡ ይዘነጋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህን ፡ በመረዳት ፡
ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ «እኔም ፡ እወዳለሁ ፡ ያለ ፡ ሐሳብ ፡
ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ሚስት ፡ የሌለው ፡ የጌታውን ፡ ነገር ፡ ያስ
ባል ፤ ጌታውን ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ዘንድ ፤ ሚስት ፡ ያለችው ፡
ግን ፡ ሚስቱን ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ዘንድ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡
ነገር ፡ ያስባል ፡ በተጋባችው ፡ ሴትና ፡ በድንግልና ፡
ባለችው ፡ ነገር ፡ የተለያየ ፡ ነው ፡ ያላገባች ፡ የእግዚአብ
ሔርን ፡ ነገር ፡ ታስባለችና ፡ ንጽሕት ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፤
በሥጋዋና ፡ በነፍስዋ ፤ የተጋባች ፡ ግን ፡ የዓለምን ፡ ነገር ፡
ታስባለች ፡ ባልዋን ፡ ደስ ፡ ታሰኝ ፡ ዘንድ ፡ » ( ፩ ፡ ቆሮ ፡
፯ ፡ ፴፪—፴፭ ፡ ) እያለ ፡ የጋብቻንና ፡ የድንግልናን ፡ ሕይ
ወት ፡ በማነጻጸርና ፡ በማመዛዘን ፡ ይናገራል ። ያላገቡ ፡
ሰዎች ፡ አለኝታቸው ፡ ተስፋቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ
ሆነ ፤ ዕጮኛቸውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ፡ ስለ
ዚህ ፡ እርሱን ፡ ለማስደሰት ፡ በጧት ፡ በማታ ፡ ይሠራሉ ፤
ጸሎት ፡ ያደርጋሉ ፤ መባዓውን ፡ እጅ ፡ መንሻውን፡ ይሰጣሉ ።



ሁል፡ ጊዜ፡ ከርሱ፡ ጋራ ፡ ይኖራሉና ፡ በዚህ ፡ ዓላማ ፡
የጸናው ፡ ድንግሉ ፡ ሁሉ ፡ የክርስቶስ ፡ እጮኛ፡ እንደ፡ ሆነ፤
ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አስረድቷል ፡ «እቀናባ
ችኋለሁና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቅናት፡ አጭቻችኋለሁና ፡ ለአ
ንድ፡ ሰው፡ ንጹሕ፡ ድንግል፡ አድርጌ ፡ ለክርስቶስ ፡ ላቀርባ
ችሁ፡ እኔ፡ ግን፡ ፈርቻለሁ፡ ምናልባት፡ እባብ፡ ሔዋንን፡ በተ
ንኰልዋ፤ እንዳሳተቻት፡ እንዲሁ፡ ሕሊናችሁ፡ እንዳትጠፉ፡
ከየውሃት፡ከንጽሕናም፡ ወደ፡ክርስቶስ፡(፪.ቆሮ፡፲፩፡፪-፫)፤ለእ
ግዚአብሔር፡ ብለው፡ ሕይወታቸውን፡ሙሉ፡በንጽሕና፡ በድ
ንግልና፡ የሚያሳልፉ፡ ፈቃደ፡ ሥጋቸውን፡ ገተው፡ እግዚአብ
ሔር፡የሚወደውን፡ሁሉ፡ በመሥራት፡ስለሚኖሩ፡ የእግዚአብ
ሔር፡ ልጆች፡ ይሆናሉ።የእግዚአብሔርንም፡ ቅዱስ፡ ፈቃድ፡
የሚፈጽመው ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ይባላልና ።
(፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፴) ። በዚህ ፡ መልክ ፡ ብዙዎች ፡ ነቢያት ፡
ሐዋርያት ፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡ ኖሩ ፡ ልዑል ፡ እግዚ
አብሔርንም ፡ በሕይወታቸው ፡ ሙሉ ፡ አገለገሉ ።

፪ኛ፤የድንግልና፡ወይም፡የብቸኝነት፡ጥቅሙ፡ማንኛውንም፡
በጎ፡ አድራጎት ፡ እንደ፡ልቡ፡ ለመፈጸም፡ እንዲችል፡ ነው ።
ባልና ፡ ሚስት ፡ በመንፈስ ፡ አንድ፡ ስለ፡ሆኑ፡ አንድ፡ አካል፡
ቢባሉም ፡ ቅሉ ፡ በተፈጥሮ ፡ ፪ ፡ መሆናቸው ፡ የታወቀ ፡
ስለ፡ሆነ ፤ ማንኛውንም ፡ ሥራ ፡ ቢሆን ፡ አንደኛው ፡ ከአ
ንዱ ፡ ተለይቶ ፡ ለመሥራት ፡ ስለማይችል ፡ ወይም፡ በቶሎ፡

www.ethiopianorthodox.org

መግባባት ፡ ስለሚያስቸግር ፤ በድንግልና ፡ ሆኖ ፡ የፈለገ
ውን ፡ በጎ ፡ አድራጎትና ፡ ርዳታ ፡ ለመፈጸም ፡ ብቻ
ውን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይችላልና ። ክርስቶስ ፡ ሲያስተምር ፡
«ቀኝህ ፡ የምታደርገውን ፡ ግራህ ፡ አትወቅብህ» ፡ ብሏል ፡
ይኸም ፡ ማለት ፡ አንተ ፡ ስትሰጥ ፡ ስትመጸውት ፡ ሚስ
ትህ ፡ ቤተ ፡ ሰብህ ፡ አይወቁብህ ፡ ሲል ፡ ነው። ከነርሱም፡
አንደኛው ፡ ተሰውሮ ፡ የሠራው፡ እንደ፡ሆነ ፤ የጋብቻውን ፡
መብትና ፡ እምነት ፡ ስለሚነካበት ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ሊፈጥ
ርበት ፡ ይችላል ፡ ይኸንም ፡ በመፍራት ፡ ከበጎ ፡ አድራ
ጎት ፡ የራቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ያለ ፡ ወቃሽ ፡ ሲያፍር ፡ ያለከ
ሳሽ፡ ሲረታ ፡ ይገኛልና ።

በድንግልና ፡ ያለው ፡ ሰው፡ ግን፡ ማንኛውንም ፡ በጎ፡
አድራጎት ፡ ሁሉ ፡ ያለችግር ፡ መፈጸም ፡ ይችላልና ፤ እን
ግዲህ ፡ በድንግልና ፡ በንጽሕና ፡ መኖር ፡ እግዚአብሔር ፡
የፈለገውን ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ ትምህርት ፡ አገልግሎት ፡ ለመ
ፈጸም ፡ ስለሚረዳ ፡ ዓላማው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ድንግሉ፡
ሰው ፡ በረሃ ፡ ቢወርድ ፤ ደጋ ፡ ቢወጣ ፤ ብርድ ፡ ወዳለበት፡
ቢሄድ ፡ ከሀገር ፡ ቢሰደድ ፤ ለሚስቱ ፡ ለልጁ ፡ አያስብም፡
የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ የሚሰፋበትን ፡ አምልኮተ፡
እግዚአብሔር ፡ የሚጸናበትን ፡ ስሙ ፡ የሚቀደስበትን ፡
ደስ ፡ ብሎት ፡ ተመችቶት ፡ ይሠራልና ። በዚህ ፡ መልክና፡
በዚህ ፡ ዓላማ ፡ ስንቱ ፡ ደናግል ፡ መነኑ ፤ በዚህ፡ ሕይወት፡



ስንቶቹ ፡ ጥቅም ፡ አስገኙ ፤ ስንትስ ፡ ነፍስ ፡ አዳኑ ፤
ስንትስ ፡ ደጋግ ፡ ነገር ፡ ሠሩ ።

፫ኛ ፤ የድንግልና ፡ ሕይወት ፡ የሚጠቅመው፡ ለወገን፡
ለሀገር ፡ ራሱን ፡ ለመሠዋት ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ ከፍ፡
ያለ ፡ ዕውቀት ፡ ኑሮት ፡ ያነን ፡ ለሕዝብ ፡ ለወገን ፡ ለማዳ
ረስ ፡ በጧት ፤ በማታ ፡ ለመሥራት ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ሙሉ ፡
ፈቃድ ፡ ለማግኘት ፡ ድንግልናን ፡ ንጽሕናን፡ ይመርጣል ።
ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ዓላማዎች ፡ በቃል፡ ቢለያዩ፡
በምሥጢርና ፡ በሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ አንድ ፡ ናቸው ።
ድንግልናም ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ ብቻ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ፡
እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሐሳብ ፡ ነፍስንም ፡ ሥጋንም ፡ ይቀድ
ሳል ፡ በዚህም፡ ዐይነት ፡ ብዙ፡ ቅዱሳን፡ ሕይወታቸውን፡
ሁሉ ፡ በድንግልና ፡ በንጽሕና፡ አሳለፉ። ከነቢያት ፡ ውስጥ፡
ትንቢት ፡ በመናገር ፡ ሱባኤ ፡ በመቍጠር ፡ ሕዝብን፡ በማ
ስተማር ፡ ሕይወታቸውን ፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡ አሳ
ለፉ ፡ ይኸውም ፡ ማዕርግና ፡ ክብር፡ ሁኗቸው ፡ እስካሁን ፡
ይጠሩበታል ፤ ይመሰገኑበታል ። ለዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ዓላማ ፡
ብለው ፡ ብዙዎች ፡ ወጣቶች፡ መነኑ፤ ከነጢያት ፡ ከፍትወ
ታት ፡ ከኃጣውእ ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ፤ ድል ፡ ነሥተውም ፡ የአቸ
ናፊነትን ፡ የንጽሕናን ፡ የድል፡ አድራጊነትን፡ ዘውድ ፡ ተቀ
ዳጁ። ለዚህ ፡ ቅዱስ ፡ ዓላማ ፡ ብለው፡ የነገሥታቱ ፡ የመሳፍ
ንቱ፡ ልጆች ፡ መነኑ ፤ የንጽሕናን ፡ የድንግልናን ፡ ሕይወት ፡

www.ethiopianorthodox.org

መረጡ ፤ መጻሕፍትን ፡ በመተርጐም ፡ ገዳማትን ፡ በማስ
ገደም ፡ ትሩፋትን ፡ በመሥራት ፡ ሕይወታቸውን ፡ አሳለፉ።
እስከ ፡ ፳ኛው ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ድንግልና ፡ ከፍ ፡
ያለ ፡ ማዕርግ ፡ ነበር ፡ ቀጥተኛ ፡ ጐዳናም ፡ በመሆኑ ፡ ብዙ
ዎች ፡ ተራመዱበት ፤ ብዙ ፡ ሥራም ፡ ሠሩበት ፤ ድንግልና ፡
የክብር ፡ ስም ፡ ነበር ። ብዙዎች ፡ ወጣቶች ፡ በዚህ ፡ ስም ፡
ለመጠራት ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ በሠለጠ
ነው ፡ ዓለም ፡ ብዙዎች ፡ በዚህ ፡ ማዕርግ ፡ በዚህም ፡ ስም ፡
ይጠቅሙበታል ፤ ይኸንም ፡ ድርጅት ፡ መልክ ፡ ሰጥተው ፡
ይሠሩበታል ፡ ሌላውም ፡ እንዲሳብ ፡ ያደርጉታል ።

የድንግልና ፡ ሕይወት ፡ የማያጋድል ፡ ታላቅ ፡ ሚዛን ፡
ነው ፤ የሰው ፡ ሕይወት ፡ በርሱ ፡ ከተመዘነ ፡ መልካሙን ፡
ውጤት ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡
ቈይቶ ፡ ባሕርዩን ፡ ከመረመረ ፡ ኑሮውን ፡ ካሻሻለ ፡ በኋላ ፡
ያገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሳይፋታ ፡ ጋብቻን ፡ አክብሮ ፡ ዓላማውን
ጠብቆ ፡ ይኖራል ። ወይም ፡ ለዘለዓለሙ ፡ በድንግልና ፡ እኖ
ራለሁ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ የገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ሳያ
ፈርስ ፡ በዚያው ፡ ጸንቶ ፡ ለመኖር ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡
ጉዳቱንና ፡ ጥቅሙን ፡ ባለማወቅ ፡ ድንግልናውን ፡ ባለመ
ጠበቅ ፡ ስድ ፡ ሆኖ ፡ የኖረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለማንኛውም ፡
ዓላማ ፡ ተስማሚ ፡ ሳይሆን ፡ ከተፈጥሮ ፡ ተራ ፡ ወጥቶ ፡
በሀገሩ ፡ ስደተኛ ፡ በሕይወቱ ፡ ፀመለኛ ፡ ሁኖ ፡ ይኖራል ።



የድንግልና ፡ ሕይወት ፡ አርቆ ፡ የሚያሳይ ፡ ከፉውን ፡ ከደግ
ለይቶ ፡ አጕልቶ ፡ የሚያሳይ ፡ መነጥር ፡ ነው ። ብዙዎች ፡
ሕገን ፡ የሚያፈርሱ ፡ ጋብቻን ፡ የሚያረክሱ ፡ የድንግልና
ቸውን ፡ ሕይወት ፡ በሚገባ ፡ ባለመጠበቃቸው ፡ የድንግል
ናን ፡ ደረጃ ፡ ባለመከተላቸው ፡ የድንግልናን ፡ ማዕርግ ፡
በማቃለላቸው ፡ ነው ።

በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡ መኖር ፡ ራስን ፡ መቈጣጠር ፡
ነው ፤ ይኸውም ፡ ለከፍተኛ ፡ ማዕርግ ፡ እንደሚያበቃ ፤ ዮሴ
ፍን ፡ ብንመለከት ፡ ለአስረጅ ፡ ያህል ፡ ይበቃናል ። ይኸ ፡ ወጣት ፡
ንጽሕናውን ፡ ለማስነካከል ፡ ከተደረገበት ፡ ታላቅ ፡ ፈተና ፡
ቢያልፍ ፡ ለጊዜው ፡ ታሰረ ፡ እንጂ ፡ ለግብጽ ፡ ገዥነት ፡
ያበቃው ፡ ቅሉ ፡ ንጽሕናው ፡ ድንግልናው ፡ ቈራጥነቱ ፡
ታማኝነቱ ፡ ነው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ አያየኝም ፡ ወይም ፡
ፍላጎቱ ፡ ከኔ ፡ ካልሆነ ፡ ብሠራውስ ፡ ምን ፡ አለብኝ ፡ ብሎ ፡
ቢያመነታ ፡ ወይም ፡ መንፈሱ ፡ ቢበረዝ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡
አሽከር ፡ ሆኖ ፡ ተዋርዶ ፡ የኋዳ ፡ ጠባቂ ፡ ሆኖ ፡ በቀረ ፡
ነበር ። «ሆዱን ፡ የወደደ ፡ ማዕርጉን ፡ ይጠላል» ፡ እንደተ
ባለው ፡ በዕለት ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ የሚታለል ፡ በዕለት ፡ አም
ሮት ፡ ብቻ ፡ የሚማረክ ፡ ሁሉ ፡ ከፍተኛ ፡ ወይም ፡ ነዋሪ ፡
ክብር ፡ አያገኝም ። ራሱን ፡ ያልተቈጣጠረና ፡ ያላስተዳደረ ፡
ሌላውን ፡ ሊያስተዳድር ፡ አይችልም ፡ ዮሴፍ ፡ ራሱን ፡ ቢቀ
ጣና ፡ ቢቈጣጠር ፡ የግብጽ ፡ ገዥና ፡ አዛዥ ፡ መሪም ፡ አስተዳ

www.ethiopianorthodox.org

ዳሪም ፡ ለመሆን ፡ በቃ። «እግዚአብሔር ፡ ከዮሴፍ ፡ ጋራ
ነበር ፤ ሥራውም ፡ ሁሉ ፡ የቀናለት ፡ ሰው ፡ ነበር » (ዘፍጥ
፴፱)፡እያለ፡ ቅዱስ፡ መጽሐፍ፡የሚያመሰግነው፡ በከንቱ፡አል
ነበረም ። ዮሴፍ፡ወጣት፡ነበር፤እንደ፡ ሰውም፡ ይበላ፡ ይጠጣ
ነበር፡ መካሪና፡ ሞግዚት ፡ እንኳን፡ አልነበረምው፡ ክፉውን
ከደግ፡ለይቶ፡ የሚያውቅ፡ ስለ፡ነበረ፡ብቻ፤ክፉውን፡ ነገር፡ሊያ
ደርግ ፡ አልፈቀደም ። ነገር ፡ ግን ፡ ቈራጥና ፡ በቀላሉ ፡ የማ
ይታለል ፡ ጀግና ፡ በመሆኑ ፡ ከዝቅተኛዪቱ ፡ ሴት፡ ሳይሆን
ከግብጽ ፡ ገዥ፡ እንደራሴ ፡ ሚስት ፡ ሊወድቅ ፡ አልቻለም
እንኳን ፡ ራሱ፡ ሊያስብና፡ ሊመኝም ፡ ቀርቶ ፡ ራሷ ፡ የሚ
ያሳፍር ፡ ነገር፡ ብትጠይቀው፡ የመለሰው፡ ቃል፡ «እንዴት
ይኽን ፡ እጅግ ፡ ክፉ፡ ነገር ፡ አደረጋለሁ ፤ በእግዚአብሔር፡
ፊትም ፡ ኀጢአት ፡ እሠራለሁ ። » (ዘፍጥ ፴፱ ፡ ፱) የሚል ፡
ነው ፤ መንፈሰ ፡ ቈራጥ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ ሁሉን ፡ በቀላሉ ፡
ድል ፡ ሊነሣ ፡ ይችላል ፤ ድንግልና ፡ አያሳፍርም ፤ አያዋር
ድም ፡ ድንግልና ፡ ይቀድሳል፡ እንጂ ፤ አያረክስም ፤ ስለዚህ፡
የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ያስብበት ፡ «በንብ ፡ ዘመን ፡ ዝንብ ፡
ይናደፋል» ፡ እንደተባለው ፤ በሕግ ፡ አፍራሽነት ፡ ዘመን ፡
እንኳን ፡ ድንግላዊ ፡ ሕይወት ፡ ጋብቻም ፡ ተነቅፎ ፡ ሁሉ ፡
ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ ለመሆን ፡ ሴራ ፡ ሲመታ ፡ ይገኛል። በዚህ፡
ነገር ፡ ከወጣቶች ፡ ይልቅ ፡ ወላጆችና ፡ ሞግዚቶች፡ ሊያስ
ቡበት ፡ ይገባቸዋል ፤ ማለት ፡ የድንግልናን ፡ የንጽሕናን ፡



ጥቅም ፡ ለወጣቶች ፡ እየነገሩ ፡ ካላሳደጓቸው ፡ ስድ ፡ ቈይ
ተው ፡ በኋላ ፡ ሊያዙ ፡ አይችሉምና ። በዚህ ፡ መንፈስ ፡
ግን ፡ ቢያሳድጓቸው፡ አንደኛውንም፡ ምርጫ፡ እስኪወስኑ ፡
ቢከተሏቸው ፡ ካገቡ፡ በኋላ ፡ ባልተፋቱም፡ ወይም ፡ አመን
ዝራ ፡ ሁነው ፡ ተፈጥሯቸውን ፡ ባላስነቀፉም ፡ ነበር ።
ግን ፡ መጥፎም ፡ ወይም፡ ደግ ፡ ነገር ፡ ቢሆን፡ ወላጆች ፡ ካላ
ሰቡበት ፡ ወጣቶች ፡ ሊጠነቀቁበት ፡ አይፈቅዱም ። በወጣ
ትነትም፡ አብሯቸው፡ ያላደገ ፡ ደግ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ እን
ግዳ ፡ እየሆነባቸው ፡ እንዲያውም፡ ቀድሞ ፡ ያላዩት ፡ አዲስ፡
ነገር ፡ ሲሆንባቸው ፡ መጥፎም ፡ ቢሆን ፡ ቅሉ ፡ የቀደመው ፡
መልካም ፡ መስሏቸው ፡ በቶሎ ፡ ሊገባቸው ፡ አይችልም ።

ም ክ ር ።

አንባቢ ፡ ሆይ ! የድንግልናን ፡ ዓላማ ፡ የድንግልናን ፡
ጥቅም ፡ ዐወቅህን ? ተረዳህን ? ፍቹንስ ፡ ትርጕሙንስ ፡ ተረ
ዳህን ? ማንኛውንም ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ለመፈጸም ፡ ኑሮ
ህን፡ ለማሻሻል ፡ ምቾት ፡ ያለው ፡ ኑሮ ፡ ለመኖር ፡ ፈልገህ ፡
እንደሆን ፡ ንጽሕናን ፡ ድንግልናን ፡ ገንዘብ ፡ አድርግ። ብዙ
ዎች ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ለሀገራቸው ፡ ፍቅር ፡ ለወገናቸው፡
ክብር ፡ ሲሉ ፡ ሕይወታቸውን ፡ በድንግልና፡ ጊዜያቸውን ፡
በሥራ ፡ አሳለፉት ፡ ስለዚህ ፡ ታሪክ ፡ ሲያስታውሳቸው ፡
ይኖራል ። ብዙዎች ፡ ቅዱሳን ፡ ለክርስቶስ ፡ ለመመስከር ፡
ለመንግሥቱ ፡ ስፋት ፡ ለአምልኮቱ ፡ ጽናት ፡ ለክርስቲያን፡

www.ethiopianorthodox.org

ብዛት ፡ ሲሉ ፡ ሕይወታቸውን ፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና
አሳለፉ ፤ ስለዚህ ፡ ሁሉን ፡ በትክክል ፡ ፈጽመው ፡ የንጽሕ
ናቸውን ፡ ዋጋ ፡ አገኙ ። አንተስ ፡ ምን ፡ ታስባለህ ፡ ሀገር
ህን ፡ ትወዳለህ ? ወገንህን ፡ ትረዳለህ ? እንዲህ ፡ ያለ ፡ ወገ
ናዊ ፡ ቅናት ፡ አለህ ? እንኪያውስ ፡ ድንግልናን ፡ ንጽሕናን
አዘውትር ፤ ገንዘብም ፡ አድርግ ፤ ሁሉ ፡ ይከናወንልህ
ዘንድ ፡ በቀንም ፡ በሌትም ፡ ለመሥራት ፡ ትችል ፡ ዘንድ
በሀብትህም ፡ በጕልበትህም ፡ ለመሥራት ፡ ትችል፡ ዘንድ።
ክርስቶስን ፡ ለመከተል ፡ ሕጉን ፡ ለመፈጸም ፡ ፈቅደሃልን ?
ለመንግሥቱ ፡ ስፋት ፡ ለክርስትና ፡ ጽናት ፡ ለክርስቲያን
ብዛት ፡ አስብሃለን ? እንኪያስ ፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና
ኑር ፡ ሁሉ ፡ ይቃናልህ፡ ዘንድ ፤ እንደ ፡ ፈቀድከውም፡ ለመ
ፈጸም ፡ ትችል ፡ ዘንድ ፤ ሕይወትህን ፡ ንጹሕ፡ መሥዋዕት
አድርገህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለማቅረብ ፡ ትችል ፡ ዘንድ
ንጽሕናን ፡ ድንግልናን ፡ አዘውትር ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ፤

## የድንግልናዊ ፡ ሕይወት ፡ ጥቅም ።

ድንግልናዊ ፡ ሕይወት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ አለው፡
ይኸውም ፡ ፩ኛ ፤ «----- እንደጸራችሁ፡ እንደ ፡ ቅዱሱ፡ እላ
ንትም ፡ ደግሞ ፡ ቅዱሳን ፡ ሁኑ ፤ በአካሄዳችሁ ፡ ሁሉ » ፡
(ዘሌዋ/ ፲፩ ፡ ፵፬ ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፭ - ፲፮) ፡ ባለው ፡ አም



ላካዊ ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ ሰውነትንም ፡ ሐሳብንም ፡ ሥራ
ንም ፡ ሁሉ ፡ ንጹሕ ፡ አድርጎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመከ
ተል ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ለማስገዛት ፡ ነው ። ለእግዚአብ
ሔርም ፡ የሚገዙ ፤ ቅዱስ ፡ ፈቃዱንም ፡ የሚፈጽሙ ፡ ሰው
ነታቸው ፡ የጠራላቸው ፡ ዕድለኞች፡ ናቸው ። ሁል፡ ጊዜ ፡
ፈጣሪያቸውን ፡ ያዩታልና ፡ « ልቡናቸው ፡ ንጹሕ ፡ የሆን ፡
ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ ያዩታልና፡ » (ማቴ ፡ ፭
፰) ። የድንግልናም ፡ ዋናው ፡ ፍቺ ፡ ራስን ፡ ከማንኛውም ፡
አምሮት ፡ ከመጥፎም ፡ ስሜት ፡ መግታት ፡ ማለት ፡ ነው ፡
እንደዚህም ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ አቸናፊነቱ ፡ ዋጋውን ፡ ከል
ውል ፡ እግዚአብሔር ፡ ያገኛልና ።

፪ኛ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውንም ፡ ዐይነት ፡
በጎ ፡ አድራጎት ፡ ለመሥራት ፡ ሙሉ ፡ ፈቃድ ፡ ፍጹም ፡
መብት ፡ እንዲያገኝ ፡ ነው ። የብቸኝነት ፡ ወይም ፡ የድንግ
ልና ፡ ሕይወት ፡ የሥራ ፡ ወይም ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ሕይ
ወት ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ ወደፈለገው ፡ አገር ፡ ለመሄድ ፡ የሚ
ፈቅደውንም ፡ ለመሥራት ፡ ለመስጠትም ፡ ቢሆን ፡ ምቹ ፡
ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ቅዱሳን ፡ አባቶች ፡
ቅዱሳት ፡ ሴቶችም ፡ ቢሆኑ ፡ ዘመናቸውን ፡ በንጽሕና ፡
በድንግልና ፡ አሳለፉ ፤ ብዙ ፡ ትሩፋትን ፡ ሠሩ ፤ ሕዝብን፡
አስተማሩ ፤ በጎ ፡ አድራጎትን ፡ ፈጸሙ ።

www.ethiopianorthodox.org

፫ኛ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ተዋሕደው ፡ ለመኖር ፡ በጢትም፡ በማታም፡ የእግዚአብሔርን፡ ቸርነት፡ በመናገር፡ ሐልዎቱን፡ በማሰብ፡ መግቦቱን፡ በማንከር፡ ለመኖር፡ ነው።

ንጽሕና ፡ በመንፈሳዊ ፡ በኩል ፡ ይህንና ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጥቅም ፡ ሲሰጥ ፡ በሥጋዊ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ እንደሚሰጥ ፡ ተመስክሮለታል ።

በአእምሮ ፡ ሕክምና ፡ በኩል ፡ ንጽሕና ፡ ድንግልና ፡ እንዴት ፡ እንደሚጠቅም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበባት ፡ ሊቃውንትን ፡ ሐሳብ ፡ እገልጣለሁ ። ኤ ፡ ክሮፕ ፡ የተባለው ፡ በሆላንድ ፡ ውስጥ ፡ ሌይዲን ፡ በተባለው ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የአእምሮ ፡ ሕክምና ፡ ፕሮፌሰር ፡ « ለወጣቱ ፡ የምሰጠው ፡ ምክር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ለፈቃደ፡ ሥጋው ፡ ነፃነትን ፡ የሚሰጥ ፡ ወጣት ፡ ወዮለት ፤ የኔርብ ፡ ሕገ ፡ ወጥነት ፡ (በሽታ) ፡ የሚፈጠረው ፡ በርሱ ፡ ምክንያት ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ ይህን ፡ አወግዛለሁ ፤ ለሰውነቱ ፡ ዕረፍትን ፡ የሰጠሁ ፡ መስሎት ፡ ዝሙት ፡ ቢሠራ ፡ በሰውነቱ ፡ ላይ ፡ ያልታወቀ ፡ ሁከትን ፡ ይፈጥራልና » ፡ እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ሊቅ ፡ ያስረዳው ፡ የድንግልና ፡ ሕይወትንም፡ ጥቅም፡ ነው ፡ ስድ ፡ በመኖሩ ፡ የሰውነቱን ፡ ሚዛን፡ ያጣል ፤ ደሙ ፡ በትክክል ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ፤ በዚህም ፡ ምክንያት፡ የኔርብ ፡ በሽታን ፡ ያመጣል ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

አብጉስት ፡ ፍሬል ፡ የተባለው ፡ የዙሪክ ፡ ፕሮፌሰር ፡ « ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ለመኖር ፡ አይቻልም ፤ ይኸውም ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይኸን፡ አጥብቆ ፡ ማወቅ ፡ አለብን ፤ ማነኛውም ፡ ወጣት ፡ እስከ ፡ ጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ ድንግልናውን ፡ መጠበቅ ፡ ግዴታው ፡ ይሆናል ፤ እንዲሁም ፡ ጠቃሚው ፡ ይሆናል ፤ ይኸውም ፡ ጥቅም ፡ በሃይማኖት ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በጤናም ፡ በኩል ፡ እንጂ » ፡ ሲል ፡ አስረድቷል ። የዚህም ፡ ሊቅ ፡ አስተያየት ፡ ዝሙትና ፡ ሴሰኝነት ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ጤንነት ፡ እንዴት ፡ እንደሚጐዱ ፡ የሚያስረዳ ፡ ነው ።



የዚህም ፡ ሊቅ ፡ ንግግር ፡ ከቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ትምህርት ፡ ጋራ ፡ ይመሳሰላል ፤ እርሱም ፡ ማንኛውንም ፡ ኀጢአት ፡ የሚሠራ ፡ ሁሉ ፡ ከሰውነቱ ፡ ውጭ ፡ ይሠራዋል ፤ ገለት ፡ ይሰርቅም ፡ ይቀማም ፡ እንደሆን ፤ ሌላም ፡ ኀጢአት ፡ ቢሠራ ፡ ቅሉ ፡ ከሰውነቱ ፡ ውጭ ፡ ይሠራዋል ፤ እንዲሁም ፡ ለጊዜው ፡ ለሥጋው ፡ ይጠቅመው ፡ ይሆናል ፤ ዝሙት ፡ የሚሠራ ፡ ግን ፡ ሰውነቱን ፡ ይበድላል ፤ ማለት ፡ ዘሩ ፡ ከአብራኩ ፡ እየተከፈለ ፡ ሲሄድ ፤ ዐቅም ፡ ያንሰዋል፤ ኀይሉም ፡ ይቀነሳል ፤ አእምሮው ፡ ይናወጣል ። ዝሙት ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ የሚያፈርሰው ፡ የእግዚአብሔርን፡ ሕግ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን፡ ሰውነቱንም፡ ያፈርሳል፤ ጤንነቱን፡ ያጣል፡ ንብረቱን ፡ ይቀንሳል ፤ « ከዝሙት ፡ ሽሹ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያደርገው ፡ ኀጢአት ፡ ሁሉ ፡ ከሰውነቱ ፡ ውጭ፡ ነው፤ የሚሰስን ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ በሰውነቱ ፡ ላይ ፡ ኀጢአትን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይሠራል» ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፰) ። በድንግልና ፡ የኖረው
ሰው ፡ ወዶ ፡ መርጦ ፡ ከአገባ ፡ በኋላ፡ ከአገባት፡ ሴት፡ ጋራ
በስምምነት ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ፤ ምክንያቱም ፡ ምን ፡ እ
ዳለ ፡ ሌላ ፡ ሊያውቅ ፡ አይችልም ፤ የሌላ ፡ ወዝ ፡ አለመ
ደም ፤ ሰውነቱን ፡ ኀይሉን ፡ ጤንነቱን ፡ አልቀነሰምና
ስለዚህ፡ ሁል፡ጊዜ ፡ ምቾትን ፡ ደስታን ፡ ገንዘብ፡ ያደርጋል
የድንግልናውም ፡ ጥቅም ፡ ይኸ ፡ ነው ። ከጤና ፤ በስምም
ነት ፡ ከመኖርና ፡ ከኑሮ ፡ ምቾት ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ በዚህ
ዓለም ፡ ሊገኝ ፡ አይችልምና ።

እንዲሁም ፡ የኒውዮርክ ፡ የሕክምና ፡ ትምህርት
ቤት ፡ የሰጠው ፡ ትምህርት ፡ « በሰዎች ፡ ላይ ፡ በዝተው
በሚገኙት ፡ ዕጢዎች ፡ ወይም ፡ የቅባት ፡ መስጫ ፡ ሕዋ
ሳት ፡ ( ግት ) ፡ ላይ ፡ ከዘር ፡ የወረደ ፡ በሽታ ፡ ሰፍሮበት
እናገኛለን ፤ ይኸውም ፡ የጋብቻን ፡ ሕግ ፡ ከመተላ
ለፍ ፡ ድንግልናን ፡ ካለመጠበቅ ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ በማ
ለት ፡ በአንድ ፡ ድምፅ ፡ ተስማምተን ፡ ንጽሕናን ፡ ድን
ግልናን ፡ ደግፈን ፡ ወስነናል ። የንጽሕና ፡ ኑሮ ፡ ለሁለት
ታላላቅ ፡ ነገሮች ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ፤ ለሰውነት ፡ ጤና
ለነፍስ ፡ ደግሞ ፡ ቅድስና »። የኒውዮርክ ፡ የሕክምና
ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሐኪሞች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምርመራ
ውጤት ፡ እንዳስረዱት ፡ ዕለትም ፡ የደረሰ ፡ ወይም፡ ከዘር
የወረደ ፡ በሽታም ፡ ቢሆን ፡ ከመቶ ፡ ፲ዘጠናው % ፡ ሕግ
በመተላለፍ ፡ የመጣ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳሉ ።



የሕዋሳትን ፡ ክፍል ፡ ባለቤቱ ፡ ሰውዬው ፡ ገልጦ ፡
ሊያየው ፡ የሚችል ፡ ቢሆን ፡ እንዴት ፡ ንጽሕናን ፡ ድንግ
ልናን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በመረጠ ፡ ነበረ ። ከጥቂት ፡ ዘመናት ፡
በፊት ፡ በብሩክሴል ፡ ተሰብስቦ ፡ የነበረው፡ የዓለም ፡ ጤና፡
ጥበቃ ፡ ኮንፈራንስ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ወስኗል ።
«የዓለም ፡ ወጣቶች ፡ በተለይም ፡ ወንዶች ፡ በንጽሕና ፡
በድንግልና ፡ እንዲኖሩ ፡ (እያንዲድጉ) ፡ የግድ ፡ ያስፈል
ጋል ፤ ድንግልና ፡ ከፍተኛ ፡ ማዕርግ ፡ ቅዱስም ፡ ትሩፋት፡
እንደ ፡ ሆነ ፤ በሕክምና ፡ ረገድ ፡ እናስረዳለን » ፡ ሲሉ ፡
ተስማሙ ።

ይኸን ፡ ቅዱስ ፡ ተግባር ፡ ሁላችን ፡ ብንፈጽመው ፡
ውጤቱን ፡ በቅርብ ፡ ለመረዳት ፡ በቻልን ፡ ነበር ፤ ማለት ፡
ግንኛውም ፡ ሰው ፡ ከሴትና ፡ ከመጠጥ ፡ ከራቀ ፤ ኀይሉ ፡
የበረታ ፡ ልቡናው ፡ የማያመነታ ፤ ጤናው፡ ያልተሰነካከለ ፤
አእምሮው ፡ የተደላደለ ፡ ግርማ ፡ ያለው ፤ በኑሮ ፡ የደላው ፡
እንደ፡ሆነ ፡ ይታወቃል፤ አሁን ፡ ዛሬ ፡ የያንዳንዱ ፡ ጤና፡ እን
ዲሁም ፡ ጠባይና ፡ ኑሮው ፡ ቢመረመር ፡ ያለዘራፊ፡ ሁሉ፡
ተወስዶበት ፡ ሁሉም ፡ ባዶው ፡ ቀፎ ፡ ሁኖ ፡ ይገኛል ።
እርሱ ፡ እንደዚህ ፡ ባለው ፡ ሕይወት ፡ ሲሰነካከል፡ ደግሞ፡
ልጆች፡ ወልዶ፡ በርሱ ፡ አስተዳደር ፡ ሲመራቸው ፡ እናገኛ

www.ethiopianorthodox.org

ለን ፤ ይህ ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ ተራ ፡ ከሰውም ፡ ግምት፡ የወጣ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ እንኳን ፡ ዘመዱን ፡ ለባዕድም ፡ ቢሆን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ማሰብ ፡ እንዳለበት ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ያስረዱናል ፤ በስም፡ ሕያው ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ቀርቶ ፡ የሞተው ፡ ነዌ ፡ እንኳ ፡ ዘመዶቼን ፡ ላስተምር ፡ ይህ ፡ መከራ ፡ ይህ ፡ ችግር እንዳይደርስባቸው ፡ ሲል ፡ እግዚብሔርን ፡ ጠይቆ ፡ ነበር፤ ያገኘው፡ መልስ፡ ግን፡ አይሰሙዋቸውም፡ እንጂ ፡ ከሰሙዋቸውስ፡ ለሕያዋን፡ ዘመዶችህ፡ ሕያዋን፡ መምህራን፡ ሕያዋን፡ መጻሕፍት ፡ አሉላቸው ፤ በአንተና ፡ በእነርሱ ፡ መካከል ፡ ግን ፡ እንዳትገናኙ ፡ ታላቅ ፡ ግድግዳ ፡ በመካከላችሁ ፡ አለ ፡ ሲል ፡ መልሶለታል ፤ (ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፳፬—፴፩)። የአእምሮ ፡ በሽታ ፡ የጠባይ ፡ ማጣት ፡ በጠቅላላውም ፡ ለዘመናዊ ፡ ሐኪሞች ፡ መድኀኒት ፡ አስቸጋሪዎች ፡ የሆኑ፡ በሽታዎች፡ የተፈጠሩ ፡ ከሕግ ፡ አፍራሽነትና ፡ ከሕገ ፡ ወጥነት ፡ ሴቱም ወንዱም ፡ ንጽሕናውን ፡ ካለመጠበቁ፡ የተነሣ፡ እንደ፡ሆነ ፡ በየጊዜው ፡ ይኸን ፡ የሚከታተሉ ፡ ሐኪሞች ፡ አስረድተዋል ። አንድ ፡ ሰው ፡ ድንግልናውን ፡ ጠብቆ ፡ ኑሮ ፡ ካላገባ ፡ የሚያጠፋው ፡ ገንዘቡን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ አእምሮውንና ፡ ጤናውን ፡ ያጠፋል ፡ እንጂ። ችግሩና ፡ በሽታው፡ ለራሱም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በልጅ ፡ ልጁም ፡ ላይ ፡ ይደርሳል ፡ ከዚህም ፡ የበለጠው ፡ መካን ፡ ይሆናል ፤ ዘር ፡ ይቀ



ንሳል ፤ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ፍጹም ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ሕግ ፡ ተቃዋሚ ፡ ይሆናል ፤ ማለት ፡ ዘር ፡ መቀነስ፡ ሀብት፡ ማሳነስ ፡ ሰይጣናዊ ፡ ሥራ ፡ ነውና ። በሀገር ፡ ላይ፡ ሰላም ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ እንዲመሠረት ፡ ዘር ፡ እንዲበዛ ፡ ወገን ፡ እንዲደረጅ ፡ የሚሠራ ፡ ፍጹም ፡ ክርስቲያናዊና ፡ የክርስቶስ ፡ ተከታይ ፡ ይሆናል ፤ ማለት ፡ የሰላም ፡ መሥራች ፡ የሰላም ፡ ባለቤት ፡ ክርስቶስ ፡ ነውና ።

ራሱን ፡ በድሎ ፡ ለሰው ፡ በደል ፡ ምክንያት ፡ የሚሆን ፡ ግን ፡ ወዮለት ፡ ወዮታም ፡ ይገባዋል ። ለወጣቶች ፡ ልጆች ፡ ዕንቅፋትና ፡ አብነት ፡ በመሆን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩትን ፡ ክርስቶስ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይገሥጻቸዋል ፤ እንዲህም ፡ ሲል ፡ ይወቅሳቸዋል ፡ ከነዚህ ፡ በኔ ካመኑት ፡ ከታናናሾቹ ፡ አንዱን ፡ ያሰነካከለ ፡ ቢኖር ፡ የድንጋይ ፡ ወፍጮ ፡ በአንገቱ ፡ አስሮ ፡ ከአዟሪ ፡ ባሕር ፡ ቢጥሉት ፡ በተሻለው ፡ ነበር ፤ (ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፮) ። በድንግልና ፡ በንጽሕና ፡ መኖር ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ እንዲገባ ፡ ክርስቶስ ፡ ራሱ ፡ ሲያስተምር ፡ « ራሳቸውን ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ብለው ፡ ጃንደረባ ፡ ያደረጉ» ሲል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡ የሚኖሩ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ እንዳላቸው ፡ መስክሯል ። ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ «የሚችል ፡ በጀመረበት ፡ ይፈጽም» ፡ብሏል ። ይህም ፡ ማለት ፡ ጋብቻን ፡ መርጦ ፡

ካገባ ፡ በዚያው ፡ ይፈጽም ፤ በድንግልናም ፡ የሚኖር ፡ የጀ
መረውን ፡ ይፈጽም ፡ ሲል ፡ ነው ። (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፬ - ፲፪) ።

ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ የንጽሕናን ፡ የድንግልናን ፡ ጥቅም ፡
ሲናገር፡ የመላእክትን ፡ ምስጋና፡ የሚሰሙ፡ ከሴት ፡ ያልረ
ከሱ ፡ ሕፃናትን ፡ አስረጅ ፡ በማድረግ ፡ ተናግሯል ። «እንደ
አዲስ ፡ ምሥጋና ፡ ያለውን ፡ በዙፋኑ ፡ ፊት ፡ በ፬ቱ ፡ እንስ
ሶችና ፡ በቀሳውስቱም ፡ ፊት ፡ ዘመሩ ፤ ማንም ፡ ያችን ፡
ዝማሬ ፡ ይማር ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፤ ከምድር ፡ ዘንድ ፡
ከተዋጁ ፡ ከመቶ ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ በቀር ። እነዚህ ፡
ናቸው ፡ ከሴቶች ፡ ጋራ ፡ ያልረከሱ፡ ድንግሎች ፡ ናቸውና ፡
በጉንም ፡ ወደሚሄድበት ፡ ሁሉ ፡ የሚከተሉ ፡ እሊህ ፡
ናቸው ፡ » (ዮሐ ፡ ራእይ ፡ ፲፬ ፡ ፫ - ፬) ።

## ምክር ።

አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ንጽሕና ፡ ድንግልና ፡ የሚረዳህን ፡
ያህል ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ አይረዳህም ፤ ማለት ፡ በንጽሕና ፡
የሚኖር ፡ ጉልበቱ ፡ አይደክም ፡ አእምሮው ፡ አይዝግ ፡
እንዲሁ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በጤና፡ ሊኖር፡ ይችላል ፤ ኀይልም፡
ካለው ፡ ዘንድ ፡ ሊሠራ ፡ ሠርቶም ፡ ሊጠቀም ፡ ይችላልና ።
ስለዚህ ፡ ንጽሕናህን ፡ ጠብቅ ፡ ወገብክን ፡ በንጽሕና ፡
ዝናር ፡ ታጠቅ ፤ በምታልፈው ፡ ዕለት ፡ የማያልፍ ፡ ስም
ህን፡ አታጥፋ። የንጽሕናን ፡ የድንግልናን፡ ጥቅም ፡ እወቅ፤
ድንግል ፡ ንጹሕ ፡ የሆንክ ፡ እንደሆነ ፡ ንብረትህ ፡ አይባ



ክን ፡ ጊዜህ ፡ በከንቱ ፡ አይጠፋ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠህ
ጸጋ ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ይሆናል ፤ የድንግልናህም ፡
ጥቅም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በበለጠ ፡ ይታወቃል ።

ከዚህ ፡ በቀር ፡ በአሁኑ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ በድንግልና ፡
በንጽሕና ፡ ሊኖርና ፡ በቀን ፡ ቀርቶ ፡ በሌሊት ፡ ሊሠራበት፡
የሚገባ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ በአንድ ፡ አገር ፡ ላይ፡
የመሸጋገሪያ ፡ ጊዜ ፡ አስቸጋሪ ፡ እንደመሆኑም ፡ መጠን ፡
ሁሉም ፡ ራሱን ፡ ወዳጅ ፡ ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ ሲሆን ፡ ብዙ ፡
ችግሮች፡ አብረው ፡ ይፈጠራሉ ፡ እንደዚያ ፡ ያለውን፡ ችግር
ሊያቃልል ፡ የሚችለው ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ የማያስበው ፡
በትዳር ፡ ላይ ፡ ያልሆነው ፡ ሕይወቱን ፡ በንጽሕና ፡ በድን
ግልና ፡ አሳልፎ ፡ ንጹሕ ፡ መሥዋዕት ፡ በማድረግ ፤ ለእግ
ዚአብሔርና ፡ ለሀገር ፡ ወይም ፡ ለወገን ፡ የሚያቀርበው ፡
ነውና ። ንጽሕናን ፡ ድንግልናን ፡ ገንዘብ ፡ በማድረግ ፡
ለሀገር ፡ መድኀኒት ፡ ለሕዝብ ፡ ምሳሌ ፡ የሆኑ ፡ ስንት ፡
ናቸው ? አንተም ፡ ከነርሱ ፡ ቍጥር ፡ ትገባ ፡ ዘንድ ፡ ይገባ
ሃል ። ንጽሕናንም ፡ ድንግልናንም ፡ ገንዘብ ፡ ታደርግ ፡
ዘንድ ፡ ይገባሃል ። የድንግልናን ፡ ሕይወት ፡ አጥብቀህ ፡
ያዝ ፤ በድንግልናህ ፡ አንተ ፡ ተጠቅመህ ፡ ሌላውን ፡ ለመ
ጥቀም ፡ ሞክር ። ንጽሕና ፡ ቀላል ፡ ዕቃ ፡ አይደለም ፡ ብዙ
ዎቹን ፡ የጠቀመ ፡ ወይም ፡ አሁንም ፡ የሚጠቅም ፡ የሰውን
እውነተኛ ፡ ደረጃውን ፡ እውነተኛ ፡ ኑሮውን ፡ የሚያረ



www.ethiopianorthodox.org

ጋግጥ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ አንተም ፡ ንጽሕናን ፡ ጠብቀህ ፡ ተጠቀምበት ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ፡ ዋጋህን፡ ታገኝ፡ ዘንድ ። የዕለት ፡ አምሮት ፡ አያሰናክልህ ፤ የዕለት፡ ስሜት፡ አያቸንፍህ ፤ የዕለት ፡ ደስታ ፡ አይኑርህ ። አንተ፡ ቀዋሚ፡ ሰው ፡ ስለ፡ ሆንክ ፡ በትንሹ ፡ አትታለል ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚቀርብህ ፡ በችግርህም ፡ የሚረዳህ ፡ ንጹሕ ፡ የሆንክ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ንጹሓን ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሁል ጊዜ፡ ያዩታል፤ ሁል፡ጊዜም ፡ ይለምኑታል ፤ እርሱም፡ ጩኸ ታቸውን ፡ ሰምቶ ፡ ሥራቸውን ፡ ተመልክቶ ፡ ይረዳቸ ዋል ፤ ለአንተም ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠባቂ ፡ ይሁንልህ ፡ አሜን ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ድንግልናዊ ፡ ሕይወት ፡ መቼ ፡ ተጀመረ ።

በድንግልና ፡ መኖር፡ መቼ ፡ እንደ ፡ ተጀመረ፡ በዚህ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የተወሰነ ፡ ዕለት ፡ ወይም ፡ ዓመት ፡ ለመጥቀስና ፡ ለማስረዳት ፡ ትንሽ ፡ ይቸግራል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ እንደምንረዳው ፡ ሁሉ ፡ አዳም ፡ ሲፈጠር ፡ የ፴ ፡ ዘመን ፡ ጐልማሳ ፡ ሁኖ ፤ ሔዋን ፡ እስክት ፈጠርለት ፡ እንዲሁ ፡ ድንግል ፡ እንደ ፡ ነበርና ፡ በድንግ ልና ፡ እንደ ፡ ኖረ ፤ ሔዋንም ፡ የሓያ ፡ አምስት ፡ ዘመን ፡ ቈንጆ ፡ ሁና ፡ እንደ ፡ ተፈጠረች ፡ ሥላሴ ፡ ለአዳም ፡ እስኪ



ሰጧት፡ ድረስ ፡ ድንግል ፡ እንደ፡ ነበረች ፤ በድንግልናም ፡ እንደ ፡ ቈየች ፡ እንረዳለን ። በድንግልና ፡ ቈይቶ ፡ በኋላ ፡ በሕግ ፡ ጋብቻ ፡ መኖሩ ፡ ሕግም ፡ መሆኑ ፡ ስለ ፡ ታወቀ ፤ ከአዳምና ፡ ከሔዋን ፡ ጀምሮ ፡ ጋብቻ ፡ በሰው ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ ይፈጸም ፡ ጀመር ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ የአዳም ፡ ፯ኛው ፡ የሚሆን ፡ ሄኖክ ፡ አግብቶ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ይዞ፡ ልጅ ፡ ወልዶ ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሁኖ ፡ እግዚ አብሔርን ፡ ደስ ፡ ሊያሰኙት ፡ ፪ቱንም ፡ ዓለም ፡ ለመው ረስ ፡ አይቻልም ፡ ብሎ ፡ የብቸኝነትን ፡ የምናኔን ፡ኑሮ፡ የን ጽሕናን ፡ ሕይወት ፡ መረጠና ፡ ያለውን ፡ ሀብትና ፡ ንብ ረት ፡ ለልጁ ፡ ለማቱሳላ ፡ ሰጥቶ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሕይ ወት ፡ ተለየ ፡ ተሰወረ ፤ የመላእክትን ፡ ሕይወት ፡ ገንዘብ አደረገ ፡ « በሃይማኖት ፡ ሄኖክ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ወጣ ፡ ሞትንም ፡ አላየም። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አልተገኘም ፤ እግዚ አብሔር ፡ አውጥቶታልና ። ሳያወጣው ፡ ተመስክሮለት ፡ ነበርና ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሰወረው ። ያለ ፡ ሃይማ ኖት ፡ ግን ፡ አይቻልም ፤ እግዚአብሔርን ፡ ያስደስት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚመጣ ፡ ይገባዋልና ፡ ያምን ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡ እንዳለ ፡ በጽኑእ ፤ ለሚሹትም ፡ ዋጋቸውን ፡ እንደሚሰጥ ፡ » ( ዘፍ ፡ ፭ ፡ ፳፬ ፤ ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፭—፮ ፡ )

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የብሕትውና ፡ ወይም ፡ የምናኔ ፡ የድንግልና ፡ ሕይወት ፡ ጀማሪው ፡ ሄኖክ ፡ ነው፡ ለማለት፡

www.ethiopianorthodox.org

በሙሉው ፡ ይቻላል ። እርሱ ፡ በዚህ ፡ ሕይወቱ ፡ ምሥጢ
ራተ ፡ እግዚአብሔርና ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ አመዳደብ ፡ ተገ
ልጦለት ፡ በስሙ ፡ የተጠራውን ፡ ይሁዳ ፡ የመሰከረለትን፡
መጽሐፍ ፡ጻፈ ፡ ( ይሁዳ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ) ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡
ከአባቶች ፡ እንዲሁም ፡ ከነቢያት ፡ ውስጥ ፡ ብዙዎቹ፡የድ
ንግልናን ፡ የብቸኝነትን ፡ ሕይወት ፡ እየመረጡ ፡ እግዚአ
ብሔርን ፡ በማገልገል ፡ ትንቢት ፡ በመናገር፡ ሱባኤ ፡ በመ
ቍጠር ፡ ሕዝብን ፡ በማስተማር ፡ ዘመናቸውን ፡ አሳለፉ ፡
ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ እነኤርምያስን ፤ እነኤልያስን ፡ እን
ጠቅሳለን ፤ ኤርምያስን ፡ «ቀደስኩከ ፡ እምከርሥ፡ እምከ፡»
ይለዋል ፡ ኤልያስንም ፡ እንዲሁ ፡ ንጹሕ ፡ ድንግል ፡
ይለዋልና ።

የእስራኤል ፡ ቈነጃጅት ፡ ብዙዎቹ ፡ ሕይወታቸውን፡
ሁሉ ፡ በድንግልና ፡ ይፈጽሙት ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ በኋላ፡
ድንግልና ፡ ፪ኛውን ፡ ደረጃ ፡ ያዘና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡
የተዋጡ ፤ በንጽሕና ፡ ያጌጡ ፡ ሁሉ ፡ የድንግልናን ፡ ሕይ
ወት ፡ ይመርጡ ፡ ጀመር ። ብዙ ፡ ደናግል ፡ ሴቶች ፡ በነበ
ሩበት ፡ ጊዜ ፡ የሐናና ፡ የኢያቄም ፡ ልጅም ፡ በድንግልና ፡
ትኖር ፡ ነበረች ፤ እርሷም ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡
ናት ። ቅድስት ፡ ማርያምን ፡ ድንግል ፡ በ፲፪ኤ ፡ ይላታል ፤
ማለት ፡ በነፍስም ፡ በሥጋም ፡ በውስጥ ፡ በአፍአም ፡ ድን



ግል ፡ ናትና ፡ ይኸም ፡ ማለት ፡ ከማየት ፡ ከመስማት፡ ከግ
ሳብ ፡ ከመሥራት ፡ ድንግል ፡ ናትና ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን
የድንግልና ፡ ሕይወት ፡ እየበረታ ፡ ሄዶ፣ ብዙ ፡ ወንዶችም፡
ሴቶችም ፡ ስለ ፡ ተነሡ ፡ የነርሱ ፡ አብነት ፡ የሆነችው ፡
ቅድስት ፡ ማርያምም ፡ የደናግል ፡ መመኪያ ፡ የደናግል ፡
ዋጋ ፡ አሰጭ ፡ የመባል ፡ ማዕርግና ፡ ስም ፡ ተሰጣት ። የቅ
ድስት ፡ ማርያምም ፡ የአክስቷ ፡ ልጅ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡
ዘመኑን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በድንግልና ፡ ካሳለፈ ፡ በኋላ ፡
እየሰበከ ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ መጣ ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡
ሁሉ ፡ ባሕርይ ፡ እንስሳዊ ፡ በሕሊናው ፡ አልወጣበትም ፡
አልወረደበትም ፡ ነበር ፤ በንጽሕና ፡ በድንግልና፡ ይኖር ፡
ነበር ፡ እንጂ ፡ ስለዚህ ፡ ሴቶች ፡ ከወለዱት ፡ ሁሉ ፡ ዮሐን
ስን ፡ የሚበልጥ ፡ የለም ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ራሱ ፡ ክርስቶስ፡
ተናገረለት ፤ ( ማቴ ፡ ፲፩ ፡ ፲፩) ።

መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ የመ
ጣበት ፡ ሰውም ፡ የሆነበት ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ ሰውን ፡ ለማ
ዳን ፡ እንጂ ፤ ለራሱ ፡ ምቾት ፡ ለራሱ ፡ ክብር ፡ ስላይደለ ፡
ለሰው ፡ ሁሉ ፡ አብነት ፡ ለመሆን ፡ ምድራዊ፡ ሕይወቱን፡
በምናኔ ፡ በዝቅተኛ ፡ ኑሮ ፡ በድንግልና፡ አሳለፈ ። የርሱም፡
ተከታዮች ፡ ሐዋርያት ፡ ፸፪ቱ፡ አርድእት፤ ፴፮ቱ፡ ቅዱሳት፡
አንስት ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ ቤት ፡ ንብረታቸውን፡ እየጣሉ፡
እርሱን ፡ ተከትለው፡ የብቸኝነትን ፡ የንጽሕናን፡ ሕይወት፡

www.ethiopianorthodox.org

አዘወተሩ ። ከነርሱም ፡ ውስጥ ፡ ያላገቡ ፡ የድንግልናን ፡
ሕይወት ፡ መርጠው ፡ የሕይወታቸውን ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡
መሥዋዕት ፡ አድርገው ፡ ለክርስቶስ ፡ ሰጡ። ክርስቶስም፡
ሲያስተምር ፡ ይደግፈው ፡ የነበረ ፡ የድንግልናን ፡ የብቸኝ
ነትን ፡ ኑሮ ፡ በመሆኑ ፡ የክርስትና ፡ ጊዜ ፡ የድንግልና ፡
የንጽሕና ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ። ለምሳሌ ፡ ክርስቶስ ፡ ከተናገራ
ቸው፡ ድንግልናዊ ፡ ሕይወትን፡ ከሚደግፉ፡ ቃላት ፡ የሚከ
ተሉት ፡ ናቸው ። « ስለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ሰውነታ
ቸውን ፡ ጃንደረባ ፡ ያደረጉ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፤ ማስተዋል ፡
የሚችል ፡ ግን ፡ ያስተውል። » (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪) ። ይኸም፡
ማለት ፡ ሥጋዊ ፡ ፈቃዳቸውን ፡ የሚገቱ ፡ ባሕርይ ፡ እንስሳ
ዊትን ፡ ከሕሊናቸው ፡ የሚያጠፉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡
መንግሥት ፡ ብቻ ፡ የሚያስቡ ፡ ሰዎች ፡ በንጽሕና ፡ በድን
ግልና ፡ ሊኖሩ ፡ እንደሚገባ ፡ የሚያስረዳ ፡ ቃል ፡ ነው ።
እንዲሁም ፡ « - - - - - - - - ቤትንም ፡ የተወ ፡ ሁሉ ፡ ወንድ
ሞችንም ፡ እኅቶችንም ፡ አባትንም ፡ እናትንም ፡ ምሽት
ንም ፡ ልጆችንም ፡ እርሻንም ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ የተወ ፡ መቶ
ዕጽፍ ፡ ይወስዳል ፤ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ ይወርሳል »
(ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፱ ) ፤ ይኸም ፡ ማለት ፡ አስቀድሞ ፡ የኑሮ ፡
ምኞትን ፡ የዓለም ፡ አምሮትን ፡ ከሕሊናው ፡ ያራቀ ፡ ለድ
ንግልና ፡ ለንጽሕና ፡ ብሎ ፡ ሚስት ፡ ማግባቱን ፡ ልጅ ፡
መውለዱን ፡ የተወ ፡ ወይም ፡ ቤት፡ ንብረት፡ ከያዘ፡ በኋላ፡



ለወንጌል ፡ ስፋት ፡ ለክርስቲያን ፡ ብዛት ፡ ለሃይማኖት ፡
ጽናት ፡ ሲል ፡ ቤቱንና ፡ ንብረቱን ፡ የተወ ፡ የዘለዓለም ፡
ሕይወትን ፡ ይወርሳል ፡ እያለ ፡ በለዘበ ፡ ቃል ፡ ያስረዳል።

ይኸንም ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ አስረጅ ፡ ይገኛል ። ሐዋ
ርያትም ፡ ይኸን ፡ ተከትለው ፡ ዘመናቸውን፡ በድንግልና፡
አሳለፉ ፤ ለሌላውም ፡ አስተማሩ ። ከነርሱም ፡ ውስጥ ፡
ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሲያስተምር ፡ « ለሰው ፡ ሴት ፡ ባይነካ፡
መልካም ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ዝሙት ፡ ከመሥራት፡ ሁሉ፡
እያንዳንዱ ፡ የምትሆነውን ፡ ያግባ ፡ - - - - » ( ፩፡ ቆሮ ፡ ፯፡
፩ ) ፡ ይኸም ፡ ማለት ፡ ቢቻል፡ ንጽሕናን፡ ጠብቆ፡ ከሴት ፡
ርቆ ፡ መኖር ፡ የበለጠ ፡ ማዕርግ ፡ የበለጠ ፡ ደረጃ ፡ የበለ
ጠም ፡ ዋጋ ፡ አለው ፡ ማለት፡ ነው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሕግ፡
ከመተላለፍ ፡ ስድም ፡ ከመሆን ፡ እያንዳንዱ ፡ የምትሆነ
ውን ፡ ያግባ ፡ ሲል ፡ ጋብቻን ፡ ፪ኛ ፡ ደረጃ ፡ አድርጎ ፡ አስ
ተማረ ። « አሁንም ፡ ይህ ፡ የሚሻል ፡ ይመስለኛል ። ስለ፡
ዘመኑ ፡ ጭንቀት ፤ እንዲህም ፡ ቢሆን ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ያም
ርበታል ። በሚስት ፡ ታስረህ ፡ እንደሆነ ፡ ከርሷ ፡ ፈጽ
መህ ፡ አትለይ ። ያለምሽት ፡ እንደ ፡ ሆንክ፡ ግን ፡ ምሽት፡
አትፈልግ ፡ - - - - እኔ ፡ ግን ፡ ያለ ፡ ሐሳብ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ፡
እወዳለሁ ። ሚስት ፡ የሌለው ፡ የጌታውን ፡ ነገር፡ ያስባል፡
ጌታውን ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ዘንድ ። ሚስት ፡ ያለችው ፡ ግን ፡
የሚስቱን ፡ ነገር ፡ ያስባል ፡ ሚስቱን፡ ደስ ፡ ያሰኝ፡ ዘንድ።

www.ethiopianorthodox.org

በተጋባችውና፡ በድንግልና፡ ባለችው፡ ነገር ፡ የተለያየነው፤ ያላገባች ፡ የእግዚአብሔርን፡ ነገር፡ ታስባለች ፤ በነፍሷም፡ በሥጋዋም ፡ ንጽሕት ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ። ያገባችው ፡ ግን ፡ የዓለምን ፡ ነገር፡ ታስባለች ፤ ባልዋን ፡ ደስ፡ ታሰኝ፡ዘንድ» ( ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፴፫ - ፴፬ ) ።

ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ የጋብቻንና፡ የድንግልናን፡ ደረጃ፡ እያበላለጠ ፡ ድንግል ፡ ሁና ፡ ቈይቶ ፡ ቢያገባ ፡ መልካም ፡ አደረገ ፡ አለና ፡ ድንግልናውን ፡ የጠበቀ ፡ ያላገባ፡ ፈጽሞ፡ የተሻለ ፡ ሠራ ፡ ሲል ፡ ድንግልናዊ ፡ ሕይወትን፡ ከፍ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የወንዶችም ፡ የሴቶችም ፡ መናንያን ፡ በመብዛታቸው ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ በሰፊው ፡ ይከናወን ፡ ነበር ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ለኔ ፡ ለራሴ ፡ የሚለውን ፡ ትቶ ፡ ለወገኔ ፡ ለሀገሬ ፡ በማለት ፡ ራሱን ፡ ስለ ፡ ሠዋ ፡ ድንግልናዊ ፡ ሕይወትንም ፡ ስለ ፡ መረጠ ፤ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በሰፊው ፡ ተቋቋሙ ፤ መጻሕፍት ፡ በሰፊው ፡ ተጻፉ ፡ ተተረጐሙም ፡ ድርሳናት ፡ ተግሣጻት ፡ ተጻፉ ፡ ገዳማት ፡ ደረጁ ፤ የጥበብም ፡ ምንጭ ፡ ሆኑ ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ራሱን ፡ ለወገኑ ፡ ለሀገሩ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ባቀረበበት ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ ንጽሕናን ፡ ድንግልናን ፡ ጠብቆ ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ርቆ ፡ ትሩፋትን ፡ ምግባራትን ፡ በሚገባ ፡ በሚፈጽምበት፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ልመናውን ፡ የሚሰማበት፡ ስጦታውን ፡ የሚቀበልበት ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ። ቅዱሳን፡ የአማላጅነት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተሰጣቸው ። እስከ ፡ ሐያኛው ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከራሱ ፡ ሕይወት ፡ ይልቅ ፡ ለሀገሩ ፡ ለወገኑ ፡ ሕይወት ፡ ለክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ ቀናተኛ ፡ ሁኖ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ቅሉ ፡ የሚገኘው ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ትምህርት ፡ መልካም ፡ ምግባርና ፡ ትሩፋት፡ ከዚያ፡ የተረፈው ፡ ነው ።



## ም ክ ር ።

አንባቢ ፡ ሆይ ፤ የድንግልና ፡ ሕይወት ፡ መቼ፡ እንደ፡ ተጀመረ ፡ ለምን ፡ እንደ ፡ ተጀመረ ፡ አይተሃል ፤ ሰምተሃል ። ጥቅሙን ፡ ዐውቀሃል ? የቀድሞ ፡ አባቶች ፡ ንጽሕናን ፡ ድንግልናን ፡ የመረጡበት ፡ ለስንፍና ፡ ወይም ፡ ራስን ፡ ብቻ ፡ ለመጥቀም ፡ አይደለም፡ ግን ፡ ራስን፡ ለሰው፡ ለማስገዛት ፤ ሀብትን ፡ ለሰው ፡ አገልግሎት ፡ ለማዋል ፡ ምቹነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ መሆኑን ፡ ዕወቅ ።

ድንግልና ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ተመሠረተ ፤ በዚህም ፡ ዓላማ ፡ ተቋቋመ ፤ በኋላም ፡ ከሰው ፡ ሕይወት ፡ ፩ኛውን ፡ ደረጃ ፡ ለመያዝ ፡ ቻለ ። በንጽሕና ፡ በድንግልና፡ የኖርክ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በበለጠ ፡ ታገለግልዋለህ ፤ ቅዱስ ፡ ፈቃዱንም ፡ ትፈጽመዋለህ ። በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡ የኖርክ ፡ እንደሆን ፡ ለሀገርህ ፡ በበለጠ ፡ ትሠራለህ፤ ሀብትህ ፡ ጒልበትህ ፡ ሰዓትህ ፡ በመላው ፡ ሕይወትህ ፡ የሀ

www.ethiopianorthodox.org

ገርህ ፡ የወገንህ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። በዚህ ፡ ዓላማ ፡ ብዙ፡ አባቶች ፡ ብዙ ፡ እናቶች ፡ ተራመዱ ፤ ግዳጅም ፡ ፈጸሙ ። አንባቢ ፡ ሆይ ፤ አንተም ፡ ተጠቀምበት፤ አንተም ፡ በዚህ፡ መምርር ፡ ተራመድበት ። ነቢዩ ፡ ሄኖክ፡ በዚህ ፡ ዓለም፡ ሁኖ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ሊያሰኙት ፡ አይችሉም ፡ ያለው ፡ ለሰውና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መገዛት፡ አይቻልም፡ ማለቱ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ የወጡ፡ ደግሞ ፡ በሕግም ፡ ሳይጸኑ፡ የድንግልናቸውንም ፡ ሕይወት ፡ አጥፍተው ፡ የሚኖሩ ፤ ይገኛሉ ፡ እነዚህ ፡ ግን ፡ አለሁ ፡ አለሁ ፤ ሲሉ ፡ የሞቱ ፡ ናቸው ። አንተ ፡ ግን ፡ ብትችል ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ድንግል ፡ ለመሆን ፡ ታገል ፡ ያለዚያም ፡ በድንግልናህ ፡ ቈይተህ ፡ የምትሆንህን ፡ በሕግ ፡ አግባ ፤ ካገባህም ፡ በኋላ ፡ ለመለየት ፡ ምክንያት ፡ አትፍጠር ፡ ይህንም ፡ ለመፈጸም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳህ ። አሜን ።

## ምዕራፍ ፡ ፳ ።

## ወ ን ድ ማ ማ ች ነ ት ።

ወንድማማች ፡ የሚለው ቃል ፡ የተገኘው ፡ ወዲውኑ ፡ የክርስትና ፡ ጮራ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሲያበራ ፡ የክርስትና ፡ ደጋፊ ፡ የሆኑ ፤ በሥጋቸው ፡ ንጽሕናን ፡ የጠበቁ ፤ ከዓለማዊ ፡ ግብር ፡ የራቁ ፤ በመንፈሳዊ ፡ ዕውቀት ፡ የጠለቁ ፡ ፍጹማን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ተነሥተው ፡ የክርስቶስ ፡



ስም ፡ በዓለም ፡ እንዲታወቅ ፡ ለመንግሥቱ፡ ስፋት ፤ ለምእመናን ፡ ብዛት ፡ ለሃይማኖት ፡ ጽናት ፡ ቈርጠው ፡ የተነሡ ፡ ሰዎች ፡ ኑሯቸውን ፡ ሐሳባቸውን ፡ ሥራቸውን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አድርገው ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፤ ይህ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ያንተ ፡ ነው ፡ ሳይሉ ፡ በአንድነት ፡ ስለ ፡ ኖሩ ፡ (የሐ፡ ሥራ፡፬፡፴፬-፴፯)፡የሚጠራሩትም፡ወንድሜ፡ወንድሜ፡እኅቴ፡ እኅቴ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ወንድማማችነት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ተፈጠረ ።

ዋናው፡ ዓላማቸው፡ ግን፡ ትምሮ፡ ማስተማር ፡ አይቶ፡ ማሳየት ፡ ሠርቶ ፡ ማሠራት ፡ በጠቅላላውም፡ ለበጎ ፡ ነገር፡ አብነት ፡ ሁኖ፡ ሌሎችን ፡ መምራት፤ ወይም ፡ በበጎ ፡ ምግባርና ፡ በፍጹም ፡ ሃይማኖት ፡ ሌላ ውን ፡ መሳብ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ውስጥ ፡ ለመጀመሪያው ፡ ጊዜ፡ የጾታ ፡ የዕድሜ፡ የማዕርግ ፡ ልዩነት ፡ ሳይኖራቸው ፤ ትንሹም ፡ ትልቁም ፡ ወንዱም ፡ ሴቱም ፡ በአንድነት ፡ ሁነው ፡ ተሰብስበው ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ መካሪ ፡ ሁነው ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ።

ይኸው ፡ ድርጅት፡ የተጀመረው ፡ በቅዱስ ፡ ጴጥሮስ፡ ስብከት ፡ ባመኑት ፡ በቅዱስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ይተዳደሩ ፡ በነበሩት ፡ ፭ቱ ፡ ሺሕ፡ ማኅበረ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ተብለው ፡ በሚጠሩት ፡ ነበር ። ይኸንም ፡ ቅዱስ ፡ ሉቃስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይመሰክርላቸዋል ፡ « የሐዋርያትን ፡ ትምህርት ፡

www.ethiopianorthodox.org

አጽንተው ፡ ይዘው ፡ የነበሩት ፡ አንድነትም ፡ እንጀራ ፡
በመቍረስ ፡ በጸሎትም ፡ ለሰውም፡ ሁሉ ፡ ፍርሀት ፡ ሆነ።
ታምራትም ፡ እጅግ ፡ ድንቅ ፡ በሐዋርያት ፡ ዘንድ ፡ ተደ
ረገ ። ያመኑትም ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ነበሩ ፡ ያላቸውም ፡ ሁሉ፡
ባንድነት ፡ ነበር ። ግዛታቸውን ፡ ጥሪታቸውንም፡ ይሸጡ
ነበሩ ። ለሁሉም ፡ ይከፍሉት ፡ ነበሩ ፤ በያንዳንዱ ፡ የሚሹ
ትን ፡ ያህል ። ዕለት ፡ ዕለትም ፡ ባንድ ፡ በመቅደስ ፡ ጸን
ተው ፡ ይኖሩ ፡ ነበሩ ፡ እንጀራም ፡ በየቤቱ ፡ ይቈርሱ ፡
ነበሩ ፡ ምግባቸውንም ፡ ይበሉ ፡ ነበሩ ። በደስታ ፡ በጽኑም፡
ልቡና ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገኑ ፡ ጸጋም ፡ ነበራቸው
በሕዝቡ፡ ፊት፡ ሁሉ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዕለት፡ ዕለት ፡ የሚ
ድኑትን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይጨምር ፡ ነበር » (የሐ.
ሥራ ፡ ፪ ፡ ፵፪ - ፵፯ ፤ ፬ ፡ ፴፪ - ፴፯) ።

ይኸም፡ ቅዱስ ፡ ተግባር ፡ ከክርስትና ፡ ጋራ ፡ በዓለም፡
ሁሉ ፡ ተዳረሰ ። በኛ ፡ ሀገር ፡ ወዲያውኑ ፡ ከክርስትና ፡
ጋራ ፡ ገባ ፡ ፲፪ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ እየተባሉ ፡ የሚጠሩት ፡ ወንድ
ማማቾች ፡ መጥተው ፡ ይኸን ፡ መንፈሳዊ ፡ አንድነት ፡
መሠረቱ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የወንድማማችነት ፡ የእኅ
ትማማችነት ፡ ማኅበር ፡ የአንድነት ፡ ኑሮ ፡ በየቦታው ፡
ተቋቋመ ። ዓላማው ፡ ደሀን ፡ በመርዳት ፡ በሽተ
ኞችን ፡ በማስታመም ፡ ትምህርት ፡ በማስተማር ፡ በጎ ፡
አድራጎትን ፡ በመፈጸም ፡ መልካም ፡ አርአያን ፡ በማሳ



የት ፡ ነበር ። ይኸንና ፡ ይኸንን ፡ የመሳሰሉትን፡ ተግባሮች፡
ስለሠሩ ፡ ክርስትናን ፡ ያላንዳች ፡ ችግር፡ ለማዳረስ፡ ቻሉ ።
ለክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ሞገስ ፡ የሰጠው ፡ በቀላሉም ፡
በዓለም ፡ ዘንድ ፡ እንዲዳረስ ፡ የረዳው ፡ ይኸ ፡ ቅዱስ ፡
ሥራ ፡ ነው ። ይኸ ፡ ወንድማማችነት ፤ ወይም ፡ የማኅበር፡
ሥራ ፡ በሀገራችን ፡ በደከመና ፡ ሁሉም ፡ ራሱን ፡ በወ
ደደ፡ ጊዜ ፡ የክርስቲያን፡ ዓላማ ፡ እየደከመ ፡ እየጠፋ ፡ ሄደ፡
ለምሳሌ ፡ የአኵስም ፡ መንግሥት ፡ ሲጠፋ ፡ ብዙ ፡ ለሀገ
ርና ፡ ለክርስትና ፡ ደገፋ ፡ የሆኑ ፡ መንፈሳውያን ፡ ተግባ
ሮች ፡ ተደምስሰው ፡ ጠፍተዋል ። ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ፡
እንደ፡ ገና ፡ በአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጊዜ ፡ መንሠራ
ራት ፡ ጀመረ ፡ ፲፪ቱ ፡ ንቡራነ ፡ እድ ፡ እየተባሉ ፡ የሚጠ
ሩት፡ የወንድማማችነትን፡ ማኅበር ፡ የአንድነትን፡ ገዳም ፡
ስለ ፡ መሠረቱ ፤ ሌላዎቹ ፡ ገዳማት ፡ ታደሱ ። የጠፋው ፡
ተገኘ፡ የሞተው፡ ተነሣ፡ ክርስትና ፡ እንደ፡ ገና፡ ተንሠራራ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ መልክ ፡ አገኘች። ምንኵስና፡ የቤተ፡
ክርስቲያን፡ ዋናው፡ ዓምድ ፡ የክርስትና ፡ ደጋፊ ፡ ከፍተኛ ፡
ድርጅት ፡ ነው ።

የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡
በወደቀችበት ፡ ጊዜ ፡ አግናጥዮስ፡ ሎይወላ፡ ተነሥቶ ፡ የወ
ንድማማችነትን ፡ ማኅበር ፡ ባያቋቁም ፡ ይኸን ፡ ጊዜ ፡ የካ
ቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፍለጋዋ፡ ባልተገኘም ፡ ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

ዛሬ፡ በዓለም ፡ ላይ፡ ለካቶሊክ ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ቀርቶ፡ በፖለቲክም ፡ አመራር ፡ ገብተው ፡ ሲሠሩ ፡ የሚገኙት ፡ ጆሱዊቶች ፡ የርሱ ፡ ግርፎች ፡ ናቸው ። በሌሎች ፡ ሀገርና፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡እንዲሁ፡ችግሩን፡የሚያቃልል፡የፈረሰውን፡የሚያድስ፡የጠፋውን፡የሚመለስ፡ይህ፡ዓይነት፡ድርጅት፡ነው፤ አንዳንድ፡ መንፈሰ፡ ቍራጦች ፡ ወንዶችም፡ ሆኑ ፡ ሴቶች ፡ ድርጅት፡ (ገዳም)፡ አቋቁመው፡ እምነታቸውን ፡ ሥርዐታቸውን ፡ የጠበቁ፡ አንዳንድ ፡ የትሩፋት፡ አበጋዞች ፡ እንዳሉ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በግሪክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ድርሰት ፡ የደረሱ፤ ተግሣጽ ፡ የጻፉ ፡ አባቶች ፡ ብዙ፡ ነበሩ ። የነርሱ ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ ዓለምን ፡ አበራ ፡ ግን ፡ በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ በነዚያ ፡ ብቻ ፡ እየተመኩ ፡ ይኸን ፡ ድርጅት ፡ ቸል ፡ ስላሉት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው፡ ከአሥጊ ፡ ሁናቴ ፡ ደርሳ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ የብዙ ፡ አባቶች፡ እናቶች ፡ ወጣቶች ፡ የአንድነት ፡ የወንድማማችነት፡ ኑሮ፡ የማኅበራዊ፡ ሥራ፡ ስለ፡ ተቋቋመ፡ «ዞይ»፡ (ሕይወት)፡ አፖስቶሊክ፡ ዲያቆኒያስ ፡ የተባለ ፡ እንዲሁም ፡ አዜልፌ ፡ ቲዎሎጎን ፡ (የመንፈሳዊ ፡ መምህራን ፡ ኅብረት) ፡ የሚሉት ፡ ይኸንም ፡ የመሰለ ፡ ዲያቆኒሳ ፡ (ዲያቆናዊት) ፡ እያሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድርጅት ፡ ስላቋቋሙ ፡ እንኳን ፡ ለሀገራቸው ፡ ለውጭውም ፡ ተርፈው ፡ ከእስያ ፡ ለጃፓን ፡ ለኮርያ ፡ ከአፍሪካ ፡ ለዩጋንዳ ፡ ተርፈው ፡ ይገኛሉ ።



በኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሁን ፡ ያለው ፡ ታላቁ ፡ ጉዳት ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ድርጅት ፡ ባለመቆሙ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ማለት፡ ሁሉም ፡ ራሱን ፡ ጠበቀ ፤ አንገቱን ፡ ቀበረ ፤ ሁሉም ፡ ለዕለት ፡ ጥቅሙ ፡ ብቻ ፡ ይሮጣል ፡ ስለዚህ ፡ ሴቲቱ ፡ ሴትነቷ ፡ እንዲታወቅ ፡ ብቻ ፡ ማግባት ፡ ግዴታ፡ ሆነ ፡ ወንዱም ፡ ለወንድነቱ፡ መታወቂያ ፡ ብቻ ፡ ማግባት፡ ግዴታ ፡ ሆነበት ፡ ወላጆችም ፡ እንዳለ ፡ የሚያምኑት ፡ ዓለም ፡ ይኸን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንዲያገቡ ፡ እየገፋፉ ፡ ያስገደዱም ፡ ሰዎች፡ አብረው ፡ እንዲኖሩ ፡ አያስገድዱም ፤ አይመክሩም ፡ ስለዚህ ፡ ሳይፈቅድ ፡ ወይም ፡ ሳትፈቅድ ፡ የተጋቡ ፡ እንዲሁም ፡ ዕድሜያቸው ፡ ስሜታቸው ፡ ለጋብቻ ፡ የማይፈቅድ ፡ በመሆናቸው ፡ በነጋው ፡ መፋታት፡ ግድ ፡ ይሆንባቸዋል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የኑሮ ፡ ዕንቅፋት ፡ ይከተላል ፤ የመለያየት ፡ መንፈስ ፡ ይፈጠራል ፡ እርስ፡ በርሷ ፡ የተለያየች ፡ አገር ፡ ትጠፋለች ፡ ብሎ፡ ክርስቶስ ፡ በአምላካዊ ፡ ቃሉ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፤ የመለያየት ፡ ውጤቱ ፡ ጥፋት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለነርሱ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለሀገርም ፡ አሥጊ ፡ ይሆናል ።

የድንግልናው ፡ ሕይወት ፡ የንጽሕናው ፡ ጊዜ፡ ለዚህ፡ ዓላማ፡ በበጀ፡ ነበር፡ የወንድማማችነትና፡ የእኅትማማችነት፡ ድርጅትም፡ ለዚህ፡ ተግባር፡ ይረዳ፡ ነበር።ለምን፡ አሁን፡ እኛ፡ አንጀምረውም? ለምንስ፡ እኛው ፡ ቈርጠን፡ አንነሣም? የሞ

www.ethiopianorthodox.org

ቱት፡ ተነሥተው ፡ እንደ፡ ማይሠሩት፡ የታወቀ፡ ነው፤የሚመ ጡትንም፡ መጠባበቅ ፡ ከሞትኩ፡ በኋላ፡ እሠራዋለሁ፡ እንደ፡ ማለት ፡ ይቈጠራል ፤ የአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የአሁኑ ፡ ሕይ ወት ፡ ብቻ ፡ ለኛ ፡ የተሰጠ ፡ ነው ፡ የአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ለዚህ ፡ ተግባር ፡ ተስማሚ ነው ። ይህ ፡ መንፈስ ፡ በኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ለመነኮሳት ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ተሰጠ ፤ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ድርጅቱ ፡ ለመቀዝቀዝ ፡ ቻለ ፡ ግን ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ፡ በድንግልና ፡ ሁነው ፡ በአንድ፡ አካባቢ ፡ የሚኖሩ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ሕይወት ፡ ያላቸው ፡ ሁሉ፡ ወንድማማች፡ እየተባሉ ፡ ብዙ ፡ ግዳጅ ፡ ፈጸሙ ። አሁን ፡ ግን ፡ እንደ ዚህ፡ ያለው ፡ ድርጅት ፡ ባለመቋቋሙ፡ ዘመድ ፡ የሌላቸው፡ ወጣቶች ፡ ራሳቸውን ፡ የሚያስጠጉበት ፡ ጊዜያቸውን ፡ የሚያሳልፉበት ፡ የተወሰነ ፡ ቦታ ፡ የተለየ ፡ ቤትም ፡ ባለ መኖሩ ፤ ኑሮዋቸው ፡ ለጋብቻ ፡ ሳይፈቅድ ፡ እንደ ፡ ሀገሩ ይኖሩ ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ አግብቶ ፡ መፍታት ፡ ግድ ፡ እየሆነባቸው ፡ በዓለማዊ ፡ ሐሳብ ፡ በጭንቀት ፡ አዘቅት ፡ ተውጠው ፡ የቀሩ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ብዙዎቹ ፡ ገዳም ፡ ካልገቡ ፡ ድንግልና ፡ የማይጠበቅ ፤ ካልመነኰሱ ፡ መን ፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ የማይሠራ ፡ እየመሰላቸው ፡ እንኳን ፡ እነ ርሱ፡ ሊሠሩት ፡ ሌላው ፡ ሲሠራ፡ ግማሹ ፡ በማድነቅ ፡ ግማ ሹም ፡ በመንቀፍ ፡ ጊዜውን ፡ ያሳልፋል ።



አሁን፡ ግን፡ የምናውጀው፤ ከፍ፡ አድርገንም፡ ጮኸን፡ አሰምተንም ፡ የምንናገረው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ እስኪ ያገባ ፡ በድንግልና ፡ መኖር ፡ ግዴታው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ካገ ባም ፡ በኋላ ፡ በሕግ ፡ ጸንቶ ፡ ማኅበራዊ፡ ሥራ ፡ መሥራት፡ የወንድማማችነትን ፡ ኅብረት ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ተግባርን ፡ መፈጸም ፡ ግዴታው ፡ እንደመሆኑና፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ ነው ።

## ም ክ ር ።

አንባቢ ፡ ሆይ ፤ የድንግልናን ፡ ሕይወት ፡ ጥቅም ፡ በመጠኑ ፡ ተረድተሃል ፡ ብዙ ፡ አገሮች ፡ የደረጁ ፡ ብዙ ፡ ሕዝቦች ፡ የሠለጠኑ ፤ አንዳንድ ፡ መንፈሰ ፡ ብርቱ ፡ እየ ተነሣ ፡ ሕይወቱን ፡ ለነርሱ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ በመስጠቱ ፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡ በመኖሩ ፡ ነው ። ብዙ ፡ ድንግሎች ፡ በአሉበት ፡ አገር ፡ የሞራል፡ ትምህርት፡ ተከብሮ ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ ተጠብቆ ፡ ይገኛል ። የሰው ፡ ሕይወት ፡ መጥፎያው ፡ ሕግ፡ መተላለፍ ፡ እንደ፡ ሆነ፤ የሰ ውም ፡ ሕይወት ፡ ሊደገፍና ፡ ሊጸና ፡ የሚችለው ፡ ድንግ ልና ፡ ንጽሕና ፡ የተጠበቀ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ አንዱ፡ ለአንዱ ፡ ሕይወቱን ፡ ቤዛ ፡ አድርጎ ፡ የሰጠ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ነው ፡ ግን ሕይወቱንም ፡ ሀብቱንም፡ ለሌላ ፡ ለማስተላለፍ ፤ ሌላውን፡ ለመደገፍ ፡ የግድ ፡ ድንግልናዊ ፡ ሕይወት ፡ ያስፈልጋል ፡ ሁሉ ፡ የቀለለ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፤ ሀብት ፡ በማጣት ፡ ወይም፡

www.ethiopianorthodox.org

በጠባዕይ ፡ ምክንያት፡ ድንግል፡ መሆን፡ የሚያሰጠው ፡ ዋጋ፡
የለውም። ድንግልና፡ቀን፡ ከሌት፡ለመሥራት፡ ይመቻል፤ ድን
ግልና፡ እንኳን፡ ሀብቱን፡ ሕይወቱን፡ ለሰው፡ ልጅ፡ አሳልፎ፡
ለመስጠት ፡ እንዲመቸውና፡ እንዲቀናው ፡ ነው። ስለዚህ ፡
በድንግልና፡ ሕይወትህ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ ፡ ተጠቀም
በት፡ ዕውቀትህን ፡ ለሌላው ፡ አካፍልበት። ሀብትህን ፡ ለደ
ሆች፡ ዕርዳበት፤ የእግዚአብሔር፡ ፍጹም፡ ተከታዩ ፤ ወይም፡
አገልጋዩ ፡ ሁን ፡ ይኸንም ፡ ለመሥራት ፡ ልዑል ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ይርዳህ ። አሜን ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

## የድንግልና ፡ ጊዜ ።

በድንግልና፡ መኖር፡ ድንግልናዊም፡ ሕይወት፡ ለሰው፡
ልጅ ፡ ለነፍስም ፡ ለሥጋም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅምን ፡ እንደ
ሚሰጥ ፡ ስንረዳ ፤ ስለ ፡ ድንግልናም፡ አስፋፍተን ፡ ስንጽፍ፡
ሁሉ ፡ በጠቅላላው ፡ ድንግል ፡ ሁኖ ፡ ድንግልናን ፡ ሁሉ ፡
አዘውትሮ፡ ብቻ፡ ይኑር፡ ማለታችን፡ አይደለም።ይኸስ፡ እን
ዳይሆን ፡ ክርስቶስ ፡ ጋብቻ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ ማግባት ፡ እንዲገባው ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ተናግሯል ።
የጋብቻን ፡ ክቡርነት ፡ የጋብቻን፡ ቅዱስነት ፡ ሲናገር፡
ከተጋቡም፡ሊፋቱ፡ እንደማይገባ፡ የተፈታውንም፡ ወገን፡ ማግ
ባት ፡ ኀጢአት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ሲያስረዳ፤ ሐዋርያት ፡ የጋብቻ፡
ነገር ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ለምን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያገባል ፡ ንጽ



ሕናን ፡ ድንግልናን ፡ አዘውትሮ ፡ አይኖርም ? የሚል ፡
ጥያቄ ፡ ባቀረቡለት ፡ ጊዜ ፤ ያገኙት ፡ መልስ ፡ ሀብተ ፡
ንጽሕ፡ ለሁሉ ፡ አይሰጥም ፡ ሁሉ ፡ በድንግልና ፡ በንጽሕና፡
ሊኖር ፡ አይቻልም ፡ ብሎ ፡ በድንግልና ፡ ሊኖሩ ፡ የሚች
ሉት፡ የተወሰኑ፡ የተመረጡ ፡ እግዚአብሔር ፡ የባረካቸው ፡
ብቻ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ዘርዝሯል ፡ «ይኸ ፡
ነገር፡ ለሰዎች፡ ሁሉ፡ አይቻልም፡ ለተሰጣቸው፡ በቀር ፡ ጃን
ደረባ ፡ ሁነው፡ ከናቶቻቸው ፡ ማሕፀን፡ የተወለዱ ፡ አሉና ፡
ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ ሰልበው ፡ ጃንደረባ ፡ ያደረጓቸው ፡
አሉና ፤ ስለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ሰውነታቸ
ውን ፡ ጃንደረባ ፡ ያደረጉ ፡ ሰዎች ፡ አሉና ፡ ማስተዋል ፡
የሚችል ፡ ግን ፡ ያስተውል» ፡ (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲፩—፲፪) ።

ይኸም ፡ ማለት ፡ ሀብተ ፡ ንጽሕ፡ ሀብተ ፡ ድንግልና፡
የሚሰጠው ፡ አለ ፤ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ዘለዓለም ፡ በንጽሕና ፡
በድንግልና ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ፡ ሌሎች ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ተወ
ሰነላቸው ፡ ዘመን ፡ ማለት ፡ ወላጆች ፡ እስከ ፡ ፈቀዱላቸው
ለዐቅመ ፡ አዳም ፡ ለዐቅመ ፡ ሔዋን ፡ እስኪደርሱ ፡ በድን
ግልና ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፤ ሊያገቡ ፡ ሕግም ፡ ሊሠሩ ፡ ቤት ፡
ንብረት ፡ ትዳር ፡ ሊይዙ ፡ ይገባል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይኸም፡
ሲሆን ፡ የድንግልና ፡ ጊዜ ፡ በ፪ ፡ ይከፈላል ፡ ማለት ፡ ነው።

፩ኛ ፤ የጊዜ ፡ ድንግልና ፤ የጊዜ ፡ ድንግልና ፡ የተባ
ለው ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከቈየ፡ በኋላ ፤ ሊያገባ ፡ የሚችል ፡

www.ethiopianorthodox.org

ነው ፡ ይኸን ፡ ዐይነት፡ ድንግልና ፡ የወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ የጊዜ ፡ ድንግልና ፡ ይባላል ። ይኸም ፡ የጊዜ ፡ ድንግልና ፡ በብዙ ፡ አኳኋን ፡ ሊጸና ፡ ይችላል ።

ሀ) ለአካለ ፡ መጠን ፡ እስኪደርስ ፤ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ዕድሜ ፡ ስለከለከለው ፡ በድንግልና ፡ መኖር ፡ የንጽሕና ፡ ጊዜውን ፡ መጠበቅ ፡ ግዴታ ፡ ስላለበት ፡ ለአካለ ፡ መጠን፡ እስኪደርስ ፡ በድንግልና ፡ መኖር ፡ ግዴታ ፡ ሲሆን ፡ የወላጆችም ፡ ፈቃድ ፡ መጨመር ፡ አለበት ፤ ማለት፡ እነርሱ፡ ሊፈቅዱና ፡ ሊከለክሉ ፡ ይችላሉና ። አንዳንድ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ልጆቻቸው፡ ለአካለ፡ መጠን፡ ሳይደርሱ ፡ ይድራሉ፤ ግን ፡ መልሰው ፡ ጋብቻውን ፡ ያስፈርሳሉ ። ይኸ ፡ እንዳይሆን ፡ ፀቱም ፡ ወገን ፡ የጋብቻውን ፡ ጥቅም ፡ እስኪያውቁ፡ መቈየት ፡ የግድ ፡ ያስፈልጋልና ፤ ያለ ፡ ዕድሜያቸው ፡ እንዲያገቡ ፡ ያስገደዱ ፡ ሰዎች ፡ ጋብቻውን ፡ እንዳያፈርሱ ፡ አያስረዱም ፡ እንዲያውም ፡ ለጋብቻው ፡ እንቅፋት ፡ እየሆኑ ፡ የድንግልናቸውን ፡ ጊዜ ፡ የሚያበላሹ፡ ጋብቻቸውን ፡ የሚያረክሱ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ወይም ፡ ወላጆች፡ አይጠፉም ።

ለ) የመንግሥት ፡ ውሳኔ ፡ ሲኖርበት ፤ ማለት ፡ በቅጣት ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ ይኖርና ፡ ያ ፡ የተወሰነው ፡ የቅጣት፡ ጊዜ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ሊያገባ፡ ስለማይችል ፤ የግድ፡ በድንግልና ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ፡ ወይም ፡ ይገደዳል ፡ የተወ



ሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈለት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ ሊያገባ ፡ ስለሚችል ፡ የጊዜ ፡ ድንግልና ፡ ተባለ ።

ሐ) የኀዘን፡ጊዜ፤ አንድ፡ሰው፡ ዕድሜው፡ወይም፡ኑሮው፡ ለጋብቻ ፡ ሲፈቅድለት፡ ሊያገባ፡ ሲዘጋጅ ፡ ቅርብ ፡ ዘመዱ፡ ወይም ፡ የሚወደው፡ ሰው ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ የኀዘኑ ፡ ወራት፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ሊያገባ ፡ አይችልም ፤ እንዲሁ ፡ በድንግልና ፡ መኖር ፡ ግዴታ ፡ ይሆንበታል ። ይኸም ፡ ውሳኔ ፡ ሊርቅም ፡ ሊቀርብም ፡ ይችላል ፤ ማለት ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፤ ቅርብ ፡ ጊዜም ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፤ ውሳኔው ፡ እንደራሱ ፡ ፍላጎት ፡ ሲሆን ፡ የኀዘኑ ፡ ወራት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ ለማግባት ፡ ነጻነት ፡ ይኖረዋል ።

መ) የኑሮ ፡ ግምቱን ፡ እስኪያውቅ ፤ ይኸም ፡ ማለት፡ ማግባት ፡ ታላቅ ፡ ሸክም ፡ በድንግልናም ፡ መኖር፡ ከባድ፡ መሆኑን ፡ ስለሚያውቅ ፡ ወደሚሻለው ፡ እስኪያዘነብልና ፡ ደንበኛ ፡ ምርጫውን ፡ እስኪያደርግ ፡ ድረስ ፡ በድንግልና ፡ ይኖራል ፤ ይኸም ፡ ሰው፡ «ሲያረጁ ፡ አንባር፡ ይዋጁ»፡ እንደተባለው፡ ሲያረጅ፡ አገባ ፡ ይሉኛል ፡ ሳይል፡ ሳይፈራ ፡ በተመቸው ፡ ጊዜ ፡ ሊያገባ ፡ ይችላል ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ስውነቱን ፡ ከመረመረ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋውን፡ ካቸነፈ ፡ በኋላ ፡ የዘለዓለም ፡ ድንግል ፡ (መነኰሴ)፡ ሊሆን፡ ይችላል ። ስለዚህ ፡ የኑሮ ፡ ግምቱን ፡ እስኪያውቅ ፡ በድን

www.ethiopianorthodox.org

ግልና ፡ ይኖራል ። ብዙ ፡ ሰው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነው ፡ ሳያ
መዛዝን ፡ እያገባ ፡ ሴቲቱም ፡ የወንዱን ፡ ወንዱም ፡ የሴቲ
ቱን ፡ ዕድል ፡ ሠባሪ ፡ እየሆነ ፡ ነው ፡ ይኸም ፡ ሊሆን ፡
የሚቻለው ፡ ራስን ፡ ባለመመርመር ፡ የኑሮ ፡ ደረጃን፡ ባለ
ማወቅ ፡ ነውና ። በድንግልና ፡ ኑረው ፡ ዐቅማቸውን ፡ ሲያ
ውቁ ፡ ሕጋቸውን ፡ አክብረው ፡ ይኖራሉ ፡ እንጂ ፤ ከተጋቡ፡
አይፋቱ ፤ አመንዝራ ፡ አይሆኑ ፤ በሽታን ፡ ችግርን ፡ ፈተ
ናን ፡ ገንዘብ ፡ አድርገው ፡ አይኖሩም ፤ ሁልጊዜ ፡ የሕይወ
ታቸው፡ ባለቤትነት ፡ እየታወሳቸው ፡ በደስታ ፡ ተውጠው
ይኖራሉና ። በዚህ ፡ ሕግ ፡ ጸንተው ፡ የዓለምን ፡ ጣዕም ፡
ዐውቀው ፡ ተደስተው ፡ የሚኖሩ ፡ ስንት ፡ ናቸው ? በቍ
ጥር ፡ የሚበዙት ፡ ግን ፡ የዕለቱን ፡ እንጂ፡ የዓመቱን ፡ ባለ
መመልከት ፡ በዕለት ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ተስበው ፡ ድንግል
ናቸውን ፡ ንጽሕናቸውን ፡ አጥፍተው ፡ በችግር ፡ በፈተና ፡
የሚኖሩ ፡ ናቸው ።

ሰ) <u>የኑሮ ፡ ደረጃው ፡ እስኪፈቅድለት</u> ፤ «ዐባይ ፡
ማደሪያ ፡ ሳይኖረው ፡ ግንድ፡ ይጐትታል» ፡ እንደተባለው፡
ድኻ ፡ ወንድ ፡ ሚስቱን ፡ በምን ፡ እንደሚረዳ ፡ ራሱንም፡
በምን ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ እንደሚያውል ፡ በምን ፡ ሁናቴ ፡
አሁን ፡ እንዳለ ፡ ሳያውቅ ፡ ሚስት ፡ ያገባል ፡ ከኑሮ ፡ ጕድ
ለት ፡ የተነሣ ፡ ፪ቱ ፡ አብሮ ፡ ለመኖር ፡ ሳይሆንላቸው ፡
ይቀርና ፡ ችግር ፡ በላያቸው ፡ ያንዣብባል ፤ ንዝንዝ ፡ ጭቅ



ጭቅ ፡ በመካከላቸው ፡ ይነሣል ፡ ይኸም ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡
በዚህ፡ ሁሉ፡ ምክንያት ፡ በቀላሉ ፡ መጋባት ፡ በቀላሉም ፡
መለያየት ፡ ደንብ ፡ ሆነ ፡ ሕግ ፡ ፈረሰ ፤ ጋብቻ ፡ ረከሰ ፤
ክርስቲያናዊ ፡ ሥርዐት ፡ ፈጽሞ፡ ተደመሰሰ ፡ ከዚህ፡ ሁሉ፡
ለመዳን ፡ ሴቲቱም ፡ ራሷን ፡ የምትረዳበት ፤ ቤቷን ፡ የም
ታስችልበት ፤ ልጅ ፡ የምታሳድግበት ፡ ሞያ ፡ ወይም ፡
ሀብት ፡ እስክታውቅ ፡ ወይም፡ እስኪኖራት፡ በድንግልና፡
መኖር ፡ ይገባታል ። ወንድየው፡ በበለጠ ፡ የቤቱ ፡ አሳዳሪ፡
መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ሚስት፡ ሲያገባ፡ እርሷ፡ ምንም፡ እንደ
ሌላት ፡ እንዴትስ ፡ እንደሚኖሩ ፡ ማጥናት ፡ ይገባል ።
ነገር ፡ ግን ፡ እርሱም ፡ ለወንድነቱ ፡ እርሷም ፡ ለሴትነቷ፡
ምልክት ፡ ብቻ ፡ የሚጋቡ ፡ ከሆነ ፡ በነጋው ፡ ልቅሶና ፡
ጫጫታ ፡ ፍቾትም ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ከዚህ ፡ ለመዳን፡
የተፈተነው ፡ መድኀኒት፡ በንጽሕና፡ በድንግልና ፡ ሁነው፡
እንደችሎታቸው፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ ንብረት፡ እያጠራቀሙ፡
ቈይተው ፡ ማግባት ፡ ነው ። ይኸ ፡ መንገድ፡ ለሰው ፡ ልጅ፡
ሁሉ ፡ ከፍ፡ ያለ ፡ ጥቅምን፡ ምቾትን ፡ ይሰጣል ። አግብቶ፡
መፍታት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ጸያፍ ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ የበለጠ
ደግሞ ፡ የተፈታውን ፡ ማግባት ፡ አመንዝራነት ፡ ነው ፤
ከዚህም ፡ አልፎ ፡ ስድነት፡ የበለጠ ፡ ሕገ ፡ ወጥነት፡ ነው።
የተፈጥሮውን ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ባለመጠበቅ፡ የንጽሕናን ፡
የድንግልናን ፡ ጥቅም ፡ ባለማወቅ ፡ በራስ ፡ ላይ ፡ በመለ

www.ethiopianorthodox.org

ገም ፡፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ሰውነቱን ፡ በመናቅ ፡ ሕይወቱን ፡
ያሳልፋል ። ማንኛውም ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ፍጥረት ፡ እስከተ
ወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ቈይቶ ፡ እንደሚያልፍ ፡ ሰውም ፡ ወደመ
ሬትነቱ፡ይመለሳል።(ዘፍጥ.፫፡፲፱፡) እግዚአብሔር፡ የሰጠው፡
ጸጋ፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ሳያውቅ፡ ሳይጠነቀቅ፡ ያሳልፈዋል።

ረ) <u>ስለ ፡ እግዚአብሔር፡ መንግሥት</u> ፤ ስለ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ መንግሥት፡ ስፋት ፡ ስለ ፡ አምልኮቱ ፡ ጽናት ፡
መንፈሳዊ ፡ ቅናት ፡ ሲኖረው ፤ በድንግልና ፡ ይኖራል ፤
ንጽሕናንም ፡ ያዘወትራል ፡ ማለት ፡ ሴትም፡ ሆነች ፡ ወንድ፡
ባለው ፡ ዕውቀቱ ፡ ወይም ፡ ሀብቱና ፡ ጕልበቱ ፡ የእግዚአ
ብሔርን ፡ ቅዱስ ፡ ፈቃድ ፡ ለመፈጸም ፡ ይመቸኛል፡ ሲል፡
የድንግልናን ፡ የንጽሕናን፡ ኑሮ፡ ይመርጣል ፤ በዚያውም ፡
ይኖራል፡ ነገር፡ ግን፡ በኋላ፡ የተወሰነው፡ ጊዜ፡ እስኪፈጸም፡
ወይም ፡ የጀመረውን ፡ ሥራ ፡ በሚገባ ፡ አጠናቆ ፡ እስኪ
ፈጽም ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ከሚ
ስቱ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ቢሠራ ፡ በበለጠ ፡ እርምጃ ፡ የሚሰ
ጠው ፡ መሆኑን ፡ አምኖ ፡ በሕግ ፡ እስኪያገባ ፡ ቤት ፡ ንብ
ረትም ፡ እስኪይዝ ፤ በድንግልና ፡ በንጽሕና ፡ ይኖራል ።
ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ የተቀደሰ ፡ ጋብቻ ፡ ሁኖ ፡
ሴቷም ፡ በባሏ ፡ ባልየውም ፡ በሚስቲቱ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
ጸንተው ፤ ደስታን ፡ ምቾትን፡ ገንዘብ፡ አድርገው፡ ይኖራሉ።
ከዚህ ፡ በላይ፡ እንደተዘረዘረው ፡ የጊዜ ፡ ድንግልና ፡ በተባ



ለው ፡ አንቀጽ፡ የተመለከቱት፡ እስከ፡ ፈቀዱት ፡ ጊዜ ፡ እስ
ከቻሉም ፡ ድረስ፡ በድንግልና ፡ ቈይተው ፡ ሊጋቡ ፡ ሙሉ፡
ፈቃድና ፡ ነፃነት ፡ አላቸው፡ እስከ፡ ተወሰነው ፡ ጊዜ፡ ግን ፡
ድንግልናን ፡ ገንዘብ ፡ ማድረግ ፡ ሰውነታቸውን ፡ መጠ
በቅ ፤ ተፈጥሯቸውን ፡ ማክበር ፤ ማዕረጋቸውን ፡ ደረጃቸ
ውን ፡ ማወቅ ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ግዴታ ፡ ነው ። በድ
ንግልና ፡ በቅድስና ፡ በንጽሕና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ እየ
ኖረ ፡ ማግባት ፡ እንዲገባው ፡ የሰው ፡ ምስክር ፡ ሳይሆን ፡
ሕግ፡ ጠባያዊ ፡ ይመሰክራል ። ስለዚህ፡ ማንኛውም ፡ ሰው፡
በመጀመሪያ ፡ በድንግልና ፡ በንጽሕና ፡ ይቈይ ፤ በኋላ ፡
ግን ፡ አረጀ ፡ አፈጀ ፡ ተብሎ ፡ ወይም ፡ ድንግልናውን ፡
አፈረሰ ፡ ሳይባል ፡ ድንግሏን ፡ ሴት ፡ ሊያገባ ፡ ወይም ፡
ድንግልናውን ፡ ለዘለዓለም ፡ ሊጠብቅ ፡ ምርጫውን ፡ በመ
ሐላ ፡ ያጸናል ፤ ሁሉም ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ ቅ፡ ጳውሎስ ፡
ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ያስረዳል ፡ «ማንም ፡ የሚሳ
ደብ ፡ ቢመስለው ፡ በድንግሉ ፡ የመጋባት ፡ ዘመን ፡ በደ
ረሰ ፡ ጊዜ ፤ እንዲሁም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ቢገባ ፡ የወደደ
ውን፡ ያድርግ ፤ ኀጢአትም፡ የለበትም ፡ ያግባ ፡ የጸና ፡ ግን፡
በልቡ ፡ ግድ ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ፡ ችሎታ፡
ያለው ፡ ይኸንንም ፡ በልቡ፡ የመረጠው፡ ድንግሉን፡ ከርሱ፡
ጋራ፡ ያለችውን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡ መልካም ፡
አደረገ። እንግዲህ ፡ ድንግሉን ፡ ለመጋባት ፡ የሰጠ ፡ መል

www.ethiopianorthodox.org

ካም ፡ አደረገ ፤ ድንግሉንም ፡ ለመጋባት ፡ ያልሰጠ ፡ ከመ ልካም ፡ የሚሻል ፡ አደረገ » (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፴፮—፴፰)

ይኸ ፡ ነገር ፡ ከባድ ፡ ያይደለ ፡ ለሁሉ ፡ የሚቀል ፤ ሩቅ ፡ ያይደለ ፡ በቅርቡ ፡ የሚሆን ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ሊራመድበት ፡ የሚገባ ፡ ለሴትም ፡ ለወንድም ፡ ልጅ ፡ ለትንሽም ፡ ለትልቅም ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ወጣቱ ፡ ራሱን ፡ ሽማግሎች ፡ ልጆቻቸውን ፡በመቈጣጠር ፡ በዚህ ፡ ጐዳና ፡ ማራመድ ፡ ይገባል ፡ በዚህ ፡ ጐዳና ፡ ሁሉ ፡ እንዲያልፉ ፡ ቢያደርጉ ፡ እንዴት ፡ ንጽሕና ፡ ቅድስና ፡ በተገኘ ፡ ሁሉ ፡ ንጹሕ ፡ ቅዱስ ፡ በሆነ ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምሕረቱ ፡ በረከቱ ፡ ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ በዝቶ ፡ በተሰጠ ።

ድንግል፡ እያልን፡ ስንናገር፡ ምናልባት ፡ ይኸ፡ ዕድል፡ ሳይገጥማቸው፡ በቂ፡ ትምህርት፡ ሳይደርሳቸው ፡ የንጽሕና ፡ ጠባያቸውን፡ ያሳደፉ፡ ቢኖሩ፤እንደ፡ ገና፡ በሕግ፡ እስኪያገቡ፡ ድረስ፡ በንጽሕና ፡ ከኖሩ ፡ ባለፈውም ፡ ከተጸጸቱና ፡ ንስሓ ፡ ከገቡ፡ ድንግል፡ ሊባሉ፡ ይችላሉ፡ ድንግልም፡ ያሰኛቸዋል ፤ ንስሓ ፡ ኀጢአተኛውን ፡ ጻድቅ ፡ ዘማዊውን ፡ ድንግል ፡ ታሰኛለች ፤ ታደርግምአለችና ፡ ይኸ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተሰጠው ፡ አስተያየት ፡ በድንግልና ፡ ቈይቶ ፡ ማግባት ፤ ከተጋቡም ፡ መፋታት ፡ የማይገባ ፡ መሆኑን ፡ ሲያስረዳ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ሳያውቁ ፡ የበደሉ ፡ የተሳሳቱም ፡ ቢኖሩ ፡



ቢመለሱና ፡ ንስሓ ፡ ቢገቡ ፡ የሚድኑ ፡ መሆናቸውን ፡ የሚገልጥ ፡ አስረጂ ፡ የሚመራ ፡ ጐዳና ፡ ሲሆን ፤ ለዘለዓለም ፤ ድንግልናን ፡ እይዛለሁ ፡ በድንግልና ፡ እኖራለሁ ፡ ካሉ ፤ ቃልም ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ ማግባት ፡ እንደማይገባ ፤ ቢያገቡ ፡ እንደሚያስፈርድ ፡ ይኸ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው፡ አስረጂ ፡ ሰሩ ፡ ያለ ፡ ወቀሳን ፡ ያመለክታል ።

«ቈነጃጅቱን ፡ ባልቴቶች ፡ ግን፡ ራሳቸውን፡ ለፍትወት ፡ ይለቃሉና ፡ ክርርቶስን ፡ ትተው ፡ ሊያገቡ ፡ ይወዳሉና ። ፍርዳቸውም ፡ ተዘጋጅቷልና ፤ የቀደመውን ፡ ብፅዓታቸውን ፡ ስለ ፡ ካዱ ። ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ተግባረ ፡ ፈትነትን ፡ ያወራሉና ፤ ቤት ፡ ለቤትም ፡ ይዞራሉና ፤ ተግባረ ፡ ፈትም ብቻ ፡ አይደለም ፡ ታዋኪዎችና ፡ ልግመኞች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፤ የማይገባ ፡ ነገርንም ፡ ይናገራሉና » (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲፩ - ፲፫) ። የዘለዓለም ፡ ድንግልና ፡ በምንኩስና ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ምንኩስና ፡ በመሃላ ፡ ሊጸና ፡ ይችላል ።

ሳይመነኰሱ፡ ድንግልናቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ መሐላ፡ ያደረጉትን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ከፍተኛውን ፡ ሸክም ፡ ለማቃለል ፡ የተወሰነ ፡ ቅዱስ ፡ ዓላማ ፡ በመሆኑ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፈቅዳው ፤ ቦታም ፡ ሰጥታው ፤ በሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም፡ አጽንታው ፡ ይዛው ፡ ትኖር ፡ ነበር። (ፍት ፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፡ ሳምን ፡ ) እንዲሁም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጸሎት ፡ ስታነሣቸው ፡ ከእኩያት ፡ ከፍትወታት ፡ ጦርነት ፡ እንዲረዳቸው ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ሞገስ ፡ ስታሰጣቸው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ትገኛለች ፤ «በእንተ ፡ ደናግል፡ ናስተበቍዕ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሀቦሙ፡ አክሊለ ፡ ድንግልና ፡ ወይኩኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውሉደ ፡ ወአዋልደ፡ ወይትወከፍ ፡ ጸመሆሙ፡ በእንተ ፡ መስተዓግሣን ፡ ናስተበቍዕ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሀቦሙ ፡ አስቦሙ ፡ በትዕግሥት ፡ ይንሥኡ ፡ ተዝከር ፡ እግዚአ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳተ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጳሳተ ፡ ቀሳስተ ፡ ወዲያቆናተ ፡ አናጕንስጢሳውያነ ፡ ወመዘምራነ ፡ ደናግለ ፡ ወመነኮሳተ ፡» እያለች ፡ ትጸልይላቸዋለች ።

ይኸ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ በወጣቱ ፡ ሕሊና፡ በሴቱም፡ በወንዱም ፡ ቢቀረጽ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በደረጀች ፡ ከድካሟ፡ በተጽናናች፡ ጉድለቷን፡ በሞላች፡ ወገኖቿም፡ በበዙ ፡ ነበር ። ይኸ ፡ መንፈስ ፡ በወጣቱ ፡ በሴቱም ፡ በወንዱም ፡ ቢቀረጽ ፡ ሁሉም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቀረበ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ጋራ ፡ በታረቀ ፡ ነበር ፡ እግዚአብሔርም፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ከሆነ ፡ ሁሉን ፡ ለማድረግ ፡ እንችላለንና ።

ከቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የሆነለት፡ እንደ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ዕድለኛ ፡ ነው ፤ ያሰበው ፡ የለመነው ፡ ሁሉ ፡ ይደረግለታልና ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ከሆነ ፡ ማን ፡ ይችለናል ? ወይስ፡ ምን ፡ ይቸግረናል፡ ሲል ፡ ተናግሯል ፡ ( ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፴፩) ።

ከዘለዓለም ፡ ድንግልና ፡ ውስጥ ፡ ድንግልናቸውን ፡ በሥራ ፡ ሥራቸውን ፡ ደግሞ ፡ በወገን ፡ ወገንነታቸውን ፡



በመለዮ ፡ የገለጡ ፡ ደናግል ፡ ንጹሐን ፡ መነኮሳት ፡ የተባሉ ፡ አሉ ፡ ይኸም ፡ ማዕርግ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከፍ፡ ያለውን ፡ ዝና ፡ ያስገኘ ፡ ለድርጅቱ ፡ የረዳ ፡ አሁንም ፡ በመርዳት፡ ላይ፡ የሚገኝ ፡ ሳይወልዱ ፡ የሚረቡ፡ በቍጥር፡ በርክተው ፡ የሚገኙ ፡ ወንበር ፡ በክታቡ ፡ መነኩሴ ፡ በቆቡ ፡ እንዲታወቅ ፡ መለዮዋቸውን ፡ በቆብ ፡ የገለጡ ፡ አሉ ። ይኸንንም ፡ በሚቀጥለው ፡ ምዕራፍ ፡ እንመረምረዋለን ።

## ም ክ ር ።

አንባቢ ፡ ሆይ ፤ የንጽሕናህን ፡ ጊዜ ፡ ጠብቅ ፤ ንጽሕና ፡ ብርታትን ፡ ይሰጣል ፤ ንጽሕና ፡ ድንግልና ፡ ውበትን ፡ የደም ፡ ግባትን ፡ መታመንን ፡ ቅልጥፍናን ፡ ይሰጣል ። ንጽሕና ፡ ከብዙ ፡ ነገር ፡ ያድናል ፡ ከብዙ ፡ ነገር ፡ ይጠብቃል ፡ ስለዚህ ፡ ሕይወትህ ፡ ወደ ፡ ጋብቻ፡ ወይም፡ ወደ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ድንግልና ፡ እስኪያዘነብል ፡ ድረስ ፡ በድንግልና ፡ በንጽሕና ፡ ኑር ፡ ማለት ፡ ጊዜያዊ ፡ ድንግልናን ፡ ያዝ ። ንጽሐ ፡ ጠባያቸው ፡ አድፎባቸው ፡ መካሪ ፡ በማጣት ፡ ከተሰነካከሉ ፡ በኋላ ፤ አሁን ፡ የሚያለቅሱ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፤ ለጊዜው ፡ ጥቅሙና ፡ ጉዳቱ ፡ አልታያቸውም ። አሁን ፡ ግን ፡ ሊመለሱባት ፡ አልቻሉም ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ባለመድረስህ ፡ ፈጣሪህን ፡ እያመሰገንህ ፡ ታገል ፡ እንጂ ፤ ለፈቃደ ፡ ሥጋህ ፡ አትገዛ ፤ እሺ፡ በጄም ፡

www.ethiopianorthodox.org

አትበለው ። ንጽሕናም ፡ ድንግልናም ፡ ስልህ ፡ የሴትና ፡ የወንድ ፡ ግብር ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ እርሱ ፡ መደበኛ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከማንኛውም ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ድንግልም ፡ ንጹሕም ፡ ሁን ። በትንሹ ፡ በኀላፊው ፡ ነገር ፡ አትታለል ፡ ካለፈ ፡ ከተሠራ ፡ በኋላ ፡ ከሚያጸጽተው ፡ ግብር ፡ ሁሉ ፡ ራቅ ። አንተ ፡ መጀመሪያ ፡ ራስህን ፡ ያወቅህ ፡ ስሜትህን ፡ ያቸነፍክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ ሌላውን፡ ልትገዛ ፡ ልታዝ ፡ ልታቸንፍም ፡ ትችላለህ ፡ ማንም፡ ሰው ፡ የሐሳቡ ፡ ጌታ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ እንጂ ፡ እርሱ ፡ ለሐሳቡ፡ የተገዛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሰውነቱ ፡ ጠባይ ፡ ፈጽሞ ፡ ይጠፉል ፤ ሰው ፡ የመባሉንም ፡ ግምት ፡ ያጣል ። ሰው ፡ የሰዎች ፡ በላይ ፡ የሚሆነው ፡ እርሱ ፡ መጀመሪያ ፡ የሐሳቡ ፡ የበላይ ፡ ገዥ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፤ በየጊዜው ፡ በሚለዋወጠው ፡ ሐሳቡ ፡ የታዘዘና ፡ የተገዛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ከሰው ፡ ተራ ፡ ይወጣል ፡ አሁንም ፡ አንተ ፡ የሐሳብህ ፡ የሕሊናህ ፡ ጌታ ፡ ሁነህ ፡ ንጽሕናን ፡ ድንግልናን ፡ አዘውትረህ ፡ ለመኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳህ ፡ አሜን ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

## የምንኵስና ፡ ሕይወት ።

ምንኵስና ፡ የኑሮ ፡ ፍልስፍና ፡ ነው ፡ ከዚህም ፡ የበለጠ ፡ አምላካዊም ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ፡ ምክንያቱም ፡ ክርስቶስ ፡ ሲያስተምር ፡ ፍጹም ፡ ልትሆን ፡ ከወደድክስ ፡ ያለህን ፡ ሁሉ ፡ ሽጠህ ፡ ተከተለኝ፡ (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ) ፡ ባለው ፡ መሠረትና ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ ቤቱን ፡ ትዳሩን ፡ የሚወድ ፡ የኔ ፡ አገልጋይ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፤ ( ማቴ ፡ ፲ ፡ ፴፯ ) ፡ ባለው ፡ የተመሠረተና ፡ የተቋቋመ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ መነኰሳት፡ የክርስቶስ፡ ተከታዮች ፡ የሕጉም ፡ ፈጻሚዎች ፡ የዓላማው ፡ ደጋፊዎችና ፡ ተባባሪዎች ፡ ናቸው ። መነኰሳት ፡ አርቀው ፡ የሚመለከቱ ፡ ፈላስፋዎች ፡ ናቸው፡ ማለት፡ ፈቃዳችንን ፡ ለሰውነታችን ፡ አናስገዛም ፤ ነፍሳችንንም፡ አንበድልም፡ በማለት፡ የቈረጡ ፡ በሐሳባቸው ፡ የሚያዙበት ፡ በዓላማቸው፡ የሚሠሩ ፡ የቈረጡ ፡ ጣዕመ ፡ ዓለምን ፡ የናቁ ፤ ምግባር ፡ ትሩፋትን ፡ ለመሥራት ፡ የታጠቁ ፡ ናቸው ፡ « ነፍሱን ፡ ሊያድናት ፡ የወደደ ፡ ይጥላታል ፤ ነፍሱን ፡ ሊጥላት ፡ የወደደ ፡ ግን ፡ ይከባከባታል» ፤ ( ማቴ ፡ ፲ ፡ ፴፱ ፤ ሉቃስ ፡ ፲፯ ፡ ፴፫ ፡ ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፳፭ ) ። እነዚህም ፡ መነኰሳት ፡ተብለው ፡ የሚጠሩ ፡ ከድንግልናዊ ፡ ሕይወት ፡ ውስጥ ፡ ፩ኛውን ፡ ከፍተኛውን ፡ የዘለዓለም ፡ ድንግልናን ፡ መርጠው በልዩ ፡ ምልክት ፡ (ቆብ) ፡ ገልጠው ፡ አስታውቀው ፡ የሚኖሩ ፡ መናንያን ፡ ናቸው ። ሥራቸውም ፡ ጸሎት ፤ ትምህርት ፤ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ነው ። የምንኵስናም ፡ የቃል



www.ethiopianorthodox.org

ፍች ፡ ከግሪክ ፡ የተወረሰ ፡ ሲሆን ፤ ፍችውም ፡ (ሞኖኮስ)፡
ብቸኛ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይኸም ፡ ድርጅት ፡ ከ፫ኛው ፡ መቶ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ፡
በዓለም ፡ የታወቀና ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አገ
ልግሎትን ፡ ያቀረበ ፤ ለክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ጌጥ፤ ለክር
ቲያናዊ ፡ ተግባር፡ ፈጻሚ ፡ ሁኖ፡ በንጽሕና ፤ በድንግልና፡
ሕይወቱን ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ የሚኖሩት ፡ ሕይወት፡
ነው ። የምንኩስና ፡ ሥርዐት ፡ ፈጥኖ ፡ በገባበት ፡ አገር ፡
ሁሉ ፡ ክርስትና ፡ በቀላሉ ፡ ለመግባት ፡ ችሏል ፤ ድርጅ
ቱም ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ቀጥሏል ፡ ምክንያቱም ፡ መነኰሳት ፡
ለራሳቸው ፡ አይሉም ፤ ቈላውን ፡ አይፈሩም ፤ ደጋውን ፡
አይሰለቹምና ፡ ነው ። ይኸ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን፡ በሐዋርያት ፡
እግር ፡ ተተክተው ፡ ክርስትና ፡ ባልደረሰበት ፡ ዓለም ፡
ሄደው ፡ የሰበኩ ፡ መነኰሳት ፡ እንደ፡ ሆኑ፡ የዓለም ፡ ቤተ፡
ክርስቲያን ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ ይመሰክርላቸዋል ። የመነ
ኰሳትም ፡ መኖሪያ ፡ የታወቀው ፡ ቦታ ፡ ገዳም ፡ ተብሎ ፡
የሚጠራው ፡ የጥበብ ፡ ምንጭ ፡ ሁኖ ፡ መጻሕፍት ፡ የተጻ
ፉበት ፤ የክርስቲያናዊ ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ መገኛ ፡ እየሆነ ፡
በዓለም ፡ ያሉትን ፡ ሕዝቦች ፡ የሚስብና ፡ የሚጐትት ፡
ነበር ። በዚህም ፡ አገልግሎት ፡ ወንዶች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡
የሴቶችም ፡ መናንያን ፡ እየበዙ ፡ በመሄዳቸው ፡ ሥርዐታ
ቸውንም ፡ ከወንዶች ፡ እኩል ፡ ከማካሄዳቸው ፡ የተነሣ ፡



በወንዶች ፡ ገዳም ፡ አንጻር ፡ የሴቶች ፡ ገዳም ፡ እየተጸጸ
ሴቶችም ፡ በበኩላቸው ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ በብ
ዛት ፡ ስላቀረቡ ፤ እንዲሁ ፡ የሴቶችን ፡ ልጆች ፡ ስሜት ፡
በአንክሮ ፡ የሚስብ ፡ የሚጐትት ፡ ሁኖ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ።

በተለይም ፡ በሮማ ፡ መንግሥት ፡ በሚተዳደሩ ፡ አገ
ሮች ፡ የክርስትና ፡ ጠላት ፡ ሁነው ፡ በሚዋጉት ፡ ውስጥ ፡
በጀግንነት ፡ መከራውን ፡ ታግሠው ፡ ተልዕኳቸውን ፡ የፈ
ጸሙት ፡ ወንዶችም ፡ ሴቶችም ፡ መናንያን ፡ መነኰሳት ፡
ነበሩ ። ስለዚህ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ቈራጥ ፡ ያደረገ ፡ የአረ
ማውያንንም ፡ ወገን ፡ ክርስትናን ፡ እንዲቀበሉ ፡ ያስጐመ
ጃቸው ፤ እነዚሁ፡ መናንያን ፡ በአኰቴት ፡ የሚቀበሉትን፡
ሥቃይ ፡ በመመልከት ፡ ነበር ።

የምንኵስና ፡ ወይም ፡ የገዳም ፡ ድርጅት፡ ሲቋቋም ፡
መነኰሳቱም ፡ ሲበዙ ፡ መተዳደሪያ ፡ ሕግ ፡ የግድ ፡ አስፈ
ለገና ፡ ብዙዎች ፡ ሊቃውንት ፡ መነኰሳት ፡ በየቦታቸው፡
ጻፉ ። ለምሳሌ ፡ አባ ፡ ጳኩሚስ ፡ በ፫፻፵፮ ፡ ዓ፡ ም ፡ ግድም፡
ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ በ፫፻፸፱ ፡ ዓ፡ ም፡ ግድም ፡ እንዲሁ ፡
ማር ፡ ይስሐቅ ፡ አረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ ፊልክስዩስ ፡ ደግ
ሞም ፡ ይኸንም ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ቀኖና ፡ ወይም ፡ ተግ
ሣጽ ፡ ጽፈው ፡ ሥርዐት ፡ ሠርተው ፡ ለተተኪዎች ፡ ያስረ
ከቡ ፡ መነኰሳት ፡ አባቶች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

፪ኛ ፤ የምንኵስናው ፡ ደረጃ ። መነኰሳት ፡ በቀድሞ ዘመን ፡ እንደ ፡ ምናኔያቸው ፡ ጽናት ፣ እንደ ፡ ትሩፋታቸው ፡ ብዛት ፡ መነኰሳት ፡ ሲባሉ ፡ ቈይተው ፡ ወደዚህ ፡ መንፈሳዊ ፡ ዓለም ፡ የሚጓዘው ፡ ሰው ፡ እየበዛ ፡ ሲሄድ ፡ ለአስተዳደሩ ፡ ልክ ፡ መልክ ፡ እንዲኖረው ፡ በማለት ፡ በመነኰሳት ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ መሠረት ፡ የምንኵስና ፡ ደረጃ ፡ ከሦስት ፡ ተከፈለ ።

ሀ) አመክሮ ፤ ይኸም ፡ ማለት ፡ በገባበት ፡ ገዳም ፡ ጥብቅ ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፣ አበውን ፡ በመርዳት ፡ ተልዕኮውን ፡ በመፈጸም ፡ እስከ ፡ ፫፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ሰውነቱን፡ በትኅርምትና ፡ በልዩ ፡ ልዩ፡ ገድል ፡ እየቀጣ ፡ ሕይወቱን፡ በፈተና፡ የሚያሳልፍ ፡ መከራውን ፡ ፈጽሞ ፡ ወደ፡ ፪ኛው፡ ደረጃ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ በሙከራ ፡ ብቻ፡ የሚቈይ፡ ነው። በዚህ ፡ ደረጃ ፡ የሚገኙት ፡ ፈተናውን ፡ ማለፍ ፡ አቅቷቸው ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ቢመለሱ ፡ እንደገናም ፡ ትዳር ፡ ለመያዝ ፡ ቢፈቅዱ ፡ የሚችሉበት ፡ ደረጃ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ወደ፡ መሐላው ፡ ያልገባና ፡ በመጀመሪያው፡ ደረጃ፡ በሙከራ ፡ የሚገኝ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ። በአመክሮ ፡ ጊዜውን ፡ የሚያሳልፍ ፡ ሰውነቱን ፡ የሚቀጣ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ራሱም ፈቅዶ ፡ ወይም ፡ በገዳሙ ፡ ሥርዐት ፡ ተገድዶ ፡ በከባድ ፡ ሥራ ፡ ተጠምዶ ፡ የተወሰነውን ፡ ቀኖና ፡ ይፈጽ



ማል ። ይኸም ፡ ማለት ፡ ገዳም ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ሁሉ ፡ የፈሪ ፡ ማንኳተቻ ፣ የደካማ ፡ መውደቂያ ፣ የሰነፍ ፡ መከማቻ ፡ አልነበረም ፣ ወይም ፡ የብጥብጥና ፡ የተንኰል ፡ ቦታ ፡ አልነበረም ፣ ወደዚያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ዓለም ፡ በፈቃድ ፡ ይመራ ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ራሱን ፡ ለመቅጣት ፣ ለመመርመር ፣ ጊዜውን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥራ፡ ለማሳለፍ፡ ከተቀደሰው ፡ ቦታና ፡ ከአበው ፡ በረከት ፡ ለመሳተፍ፣ ስለነበር ፡ ነው ። ይኸን ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ በዚህ፡ ቅዱስ፡ ተግባር ፡ ካሳለፉ ፡ በኋላ ፡ አበ ፡ ምኔቱ ፡ የሃይማኖቱን ፡ ጽናት ፣ የምግባሩን ፡ ቀናነት ፣ የትሩፋቱን ፡ ብዛት ፡አይቶ ወደ፡ ምትበልጥ ፡ ማዕርግ ፡ ወደ ፡ ምንኵስና፡ ያስገባዋል ፣ ይኸውም ፡ የመነኰሳት ፡ መለያ ፡ የሚሆነውን ፡ ቆቡን ፡ ይደፋለታል ፤ ቀሚስ ፡ ያለብሰዋል ፤ የተለየ ፡ ጸሎት ፡ ያደርግለታል ፣ ከመነኰሳቱም ፡ አንድ ፡ ተብሎ፡ ይቈጠራል። አንዳንዶችም ፡ ለማዕርገ ፡ ምንኵስና፡ የማይቸኩሉ፡ የመከራውን ፡ ጊዜ ፡ ሳይወስኑ ፡ ዕድሜያቸውን ፡ በዚሁ ፡ የሚያሳልፉ ፡ አሉ ።

ለ) ምንኵስና ፤ በዚህ ፡ ማዕርግ ፡ ያሉት ፡ ከላይ፡ እንተነገረው ፡ ሁሉ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ፈጽሞ ፡ የተለየሁ ፡ ነኝ፡ ፪ኛ ፡ ወደ ፡ ዓለማዊ ፡ ግብር ፡ አልመለስም ፤ ዓለሙ ፡ በኔ ዘንድ፡ የሞተ፡ ነው፤ እኔም፡ በዓለሙ፡ ዘንድ፡ የሞትኩ፡ ነኝ፡ ሲል፡ መሐላውን፡ የእግዚአብሔርን፡ ስም፡ በመጥራት፡ ይፈ

www.ethiopianorthodox.org

ጽማል ፤ ቃል ፡ ኪዳንም ፡ ይገባል ። ለዚህ ፡ መለያ ፡ ቆቡን ፡ ይደፋል ፤ ይኸም ፡ ክርስቶስ ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ የተቀዳጀው ፡ የአክሊለ ፡ ሶኩ ፡ (የሾሁ ፡ አክሊል ፡) ምሳሌ ፡ ነው ፡ ለመንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ለገዳሙ ፡ ተልዕኮት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከመምህሩ ፡ ፈቃድ ፡ ሳያገኝ ፡ ከበአቱ ፡ እንዳይወጣ ፡ ቃል ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡ አእምሮው ፡ ስፋት ፡ እንደ ፡ ምግባሩ ፡ ችሎት ፡ ሥራ ፡ ተሰጥቶት ፡ ይኖራል ። ይኸም ፡ መነኰሴው ፡ የገባበት ፡ ዓለም ፡ ዓለመ ፡ መላእክት ፡ ይባላል ፡ ሰዎቹም ፡ መላእክት ፡ ዘበምድር ፡ ወሰብእ ፡ ሰማያውያን ፡ ይባላሉ ፤ ማለት ፡ በምድር ፡ ያሉ ፡ መላእክት ፡ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ማለት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ባለመኖራቸው ፡ ቈላውን ፡ ደጋውን ፡ ባለመፍራታቸው ፡ የሰው ፡ ወይም ፡ የባዕድ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ሳይሉ ፡ በማስተማራቸው ፡ ሐዋርያትን ፡ ወይም ፡ መምህራቸውን ፡ ክርስቶስን ፡ የመሰሉና ፡ የተከተሉ ፡ ናቸው ።

ሐ) <u>የፍጹማን ፡ ማዕርግ ፡ አስኬማ</u> ፤ ከላይ ፡ የተነገሩትን ፡ በትክክል ፡ ፈጽሞ ፡ በዕድሜው ፡ የገፋ ፤ የምግባር ፡ ስልቶችን ፡ ጠንቅቆ ፡ ያወቀ ፡ ሥርዐተ ፡ ገዳሙን ፡ የጠበቀ ፡ አንዳች ፡ ነቀፋ ፡ ያልተገኘበት ፡ አባት ፡ መነኰሴ ፡ አስኬማ ፡ የተባለውን ፡ ማዕርግ ፡ ፫ኛውን ፡ ደረጃ ፡ ያገኛል ። አስኬማ ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ (እስኪማ) የግሪክ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ፍችው ፡ ምልክት ፡ ማለት ፡ ነው ። ከፍተኛ ፡



ምልክት ፡ ብዙ ፡ መስቀል ፡ ያለበት ፡ ለባስያነ ፡ መስቀል ፡ የሚያሰኛቸው ፡ ፍጹማን ፡ የሆኑ ፡ መነኰሳት ፡ ብቻ ፡ የሚያገኙት ፡ ማዕርግ ፡ ነው ። ይኸን ፡ ማዕርግ ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ አይወጡም ፡ የላመ ፡ የጣመ ፡ አይቀምሱ ፤ ከክፉ ፡ ነገር ፡ አይደርሱ ፤ ጊዜያቸውን ፡ ለምስጋና ፡ ብቻ ፡ ሰጥተው ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ። ከዚህ ፡ ማዕርግ ፡ የደረሱ ፡ አባቶች ፡ ምግባቸው ፡ የተወሰነ ፡ ሁኖ ፡ እንቅልፍ ፡ እንዳገኙ ፡ አይተኙም ፤ እንዲሁ ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ ሰላም ፤ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ኀጢአት ፡ ይቅርታ ፡ ይጸልያሉ ።

በገዳሙ ፡ ለሚኖሩ ፡ መናንያን ፡ የሚናዝዙ ፡ እንደ ፡ ንስሓ ፡ አባት ፡ ሁነው ፡ የሁሉን ፡ ሸክም ፡ የሚያቀሉ ፡ ፍጹማን ፡ ናቸው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘረው ፡ ማዕርግ ፡ በካህን ፡ መነኰሴ ፡ በጨዋ ፡ ባልተማረ ፡ መነኰሴ ፡ በሴት ፡ መነኰሲት ፡ ሁሉ ፡ አሰጣጡ ፡ ትክክል ፡ ነው ። በዚህ ፡ ደረጃ ፡ ካልሄደ ፡ ምንኵስና ፡ ሊሰጥ ፡ አይቻልም ። ቢሰጥም ፡ ዋጋ ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ፤ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ ለምሳሌ ፡ አልፎ ፡ ሂያጁ ፡ ሁሉ ፡ አመንኵሱኝ ፡ ሲል ፡ የት ፡ ነበርክ? ለምን ፡ መጣህ ? ለምንስ ፡ ምንኵስናን ፡ ፈለግህ ? ሳይሉ ፡ ሳይመረምሩ ፡ ቆብ ፡ ይጭኑባቸዋል ፡ በነጋው ፡ መለመኛ ፡ አድርገውት ፡ ሰውን ፡ በመርዳት ፡ ፈንታ ፡ ርዱን ፡ ሲሉ ፡ በተወሰነ ፡ ቦታ ፡ በመቀመጥ ፡ ፈንታ ፡ ገጠሩ ፡ ከተማው ፡

www.ethiopianorthodox.org

አልበቃቸው ፡ ብሎ ፡ ሲዞሩ ፡ ገዳሙንና ፡ ምንኩስናን ፡ ሲያሰድቡ ፡ ይገኛሉ ። ይኽም ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ የዚህ ፡ ጥናት ፡ በአመንኳሹም፡ በመንኳሹም ፡ ዘንድ ፡ ያልተጠና ፡ በመሆኑ ፡ እንዲሁ ፡ በልማድ ፡ ብቻ ፡ በመሠራቱ ፡ ነው ።

፩ኛ ፤ ወደ ፡ ገዳም ፡ ለመግባት ፡ የሚችሉት ፤ በቀድሞ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ፍጹም ፡ ነጻነቱ ፡ ስላልተረጋገጠ ፡ የባሪያ ፡ መሸጥ ፡ መለወጥ ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ ለነርሱ ፡ ይኽ ፡ ዕድል ፡ አይሰጣቸውም፡ ነበር ፤ ማለት ፡ ገዳሙ ፡ አይቀበላቸውም ፡ የማለት ፡ ሳይሆን ፤ እነርሱ ፡ አይችሉም ፡ ነበር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ገዳማት ፡ የሚገኙባቸው ፡ ቦታዎች ፡ እሩቅ ፡ በመሆናቸው ፡ አገልጋዮች ፡ እንደ፡ ልባቸው፡ ብቻ ቸውን ፡ ሊሄዱ ፡ አይችሉም ፡ ነበር ፡ እንደ ፡ ማንም ፡ ብሎ፡ የገባ ፡ ግን ፡ ዕድል ፡ ገጥሞት ፡ ከገባ ፡ አይወጣም ፡ ነበር ፤ «ገዳም ፡ የገባ ፡ አይወጣ ፤ ከል ፡ የገባ ፡ አይነጣ » ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ እንዲሁ ፡ ከአበው ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ እየተቈጠረ ፡ ሊኖር ፡ ይችል ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ የልጅነት ፡ ዕድሜ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ለትምህርት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በገዳም፡ እንዲቀመጡ ፡ አይፈቀድላቸውም ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ገዳማት፡ የጥበባት ፡ የትምህርትም ፡ ምንጮች ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ የትልልቅ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ልጆች ፡ ሳይቀሩ ፡ ከዚያ ፡ እየ ገቡ ፡ ይማሩ ፡ ሥርዐተ ፡ ገዳሙንም ፡ ይከታተሉ ፡ ነበር ፤ በዚህም፡ ምክንያት ፡ በዚያው፡ መንነው፡ የሚቀሩ ፡ ነበሩ ፤



ትምህርታቸውን ፡ ፈጽመው ፡ ቢመለሱም ፡ ለድኻ ፡ የሚ ያዝኑ ፡ የሚራሩ ፤ ፍርድ ፡ ጐደለ ፡ ድኻ ፡ ተበደለ ፡ ብለው፡ የሚያዝኑ ፤ መንፈሳዊ ፡ ስሜት፡ በብዛት ፡ ያላቸው፡ ነበሩ።

ወደ ፡ ገዳም ፡ ሊገባ፡ የሚገባው ፡ መካከለኛ ፡ ዕድሜ፡ ያለው ፡ ክፉውን ፡ ከደግ ፡ ለይቶ ፡ ያወቀ ፤ ራሱን ፡ የመረ መረ ፤ ኃይለ ፡ ሥጋው ፡ ያልበረደ ፤ አበውን ፡ ለመርዳት ፡ ገዳሙን ፡ ለማደርጀት ፡ በጎ ፡ ፈቃድና ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ነበር ።

እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቈርጦ ፡ ከገባ ፡ አይ ወጣም ፤ የጀመረውን ፡ ሥራ ፡ አያቋርጥም ፡ ነበር ፤

አሁን ፡ ግን ፡ ፪ኛ ፡ ለገዳሙ ፡ ሸክም ፡ ለመሆን ፡ ጧሪ ፡ ሲያጡ ፡ ጉልበታቸው ፡ ሲደክም ፡ ገዳም ፡ ይገ ባሉ ፡ ተቀምጠው ፡ እንዳይጠሩም ፡ «የተቀማጭ ፡ አፉ ፡ ምላጭ» ፡ እንደተባለው ፡ ሁሉ ፤ በገመድ ፡ ፈንታ ፡ ነገር ፡ ሲጐነጉኑና ፡ ሲፈትሉ ፡ የገዳሙን ፡ መልክ ፡ ሲለውጡ ፡ ይገኛሉ ። እንዲሁም ፡ ግማሾቹ ፡ በሕፃንነት ፡ ዕድሜያ ቸው ፡ ይገቡና ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ የፍጹም ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ ቈይተው ፡ አእምሮ ፡ ሲያውቁ ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ወደ፡ ከተማ ፡ መዛወር፡ ይጀምራሉ ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ብዙዎችን ፡ ድቀት ፡ ሊያገኛቸው ፡ ይችላል ። ብዙዎቹ ፡ ደግሞ ፡ ይኸኑ ፡ ሥራ፡ አድርገው ፡ ገዳምንም ፡ ምንኵስና ንም ፡ ሲያሰድቡ ፡ ይኖራሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

<u>፩ኛ ፤ ገዳም</u> ፤ የምንኵስናን ፡ ነገር፡ ከተናገርን ፡ ዘንድ፡
የመነኰሳት ፡ መኖሪያ ፡ የሆነውን ፡ የቅዱሱን፡ ቦታ፡ የስም፡
ዝርዝር ፡ መናገር ፡ ግዴታ ፡ ይሆናል ፤ ገዳም ፡ ማለት ፡
በመሠረቱ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እንዲሁም ፡
ጫካው ፡ የበዛበት ፤ ድምፀ ፡ አራዊት ፡ ግርማ ፡ ሌሊቱ ፡
የበዛበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፤ ወይም ፡ ቅጠል ፡ ዛፍ ፡ የሌለበት ፡
የምንም ፡ ድምፅ ፡ የማይሰማበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡
ገዳም ፡ ይባላል ። መነኰሳት ፡ እየመነኑ ፡ ይኸን ፡ የመ
ስለ ፡ ቦታ ፡ እየፈለጉ ፡ ሄደው፡ ስለ፡ ተቀመጡበት፡ ከቀን፡
ብዛት፡ መነኰሳት ፡ እየበዙ ፡ ድርጅቱ ፡ እያማረ ፡ ጫካው፡
እየቀና ፤ ምድረ ፡ በዳው ፡ ዛፍ ፡ እየተተከለበት ፡ የአውሬ ፡
ድምፅ ፡ ብቻ ፡ ይሰማበት ፡ የነበር ፡ ቦታ ፡ የመነኰሳቱ ፡
ውዳሴ፡ ቅዳሴ፡ ምስጋና ፡ የሚሰማበት ፡ ስለ፡ ሆነ ፤ ገዳም ፡
ተባለ፤ ማለት፡ አሁን፡ ገዳም፡ ተለውጦ፡ የጽድቅ፡ ቦታ፡ ቃል፡
ኪዳን፡ ያለበት ፡ ሕዝብ ፡ በረከት ፡ ረድኤት ፡ የሚያገኝበት፡
መንግሥት ፡ ያከበረው ፡ ሕዝብ ፡ ያወቀው ፡ ትልቅ ፡ ቦታ፡
ትልቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ይኸም ፡ ይታ
ወቅ፡ ዘንድ፡ የእገሌ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ተገደመ ፡ ሲባል፡
ተከበረ ፤ ታወቀ ፡ ማለት ፡ ነው ። ገዳም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡
በሩቅ ፡ ቦታ ፡ ብቻ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ለውሃውና ፡ ለአትክ
ልት ፡ ቦታ ፡ ተስማሚ ፡ የሚሆን ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ሲገኝ ፤
ደጋጎች ፡ ነገሥታት ፡ እየመረጡ ፡ ገዳም ፡ እየተከሉበት ፡
መተዳደሪያቸውን ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡



ብዙዎቹ ፡ ገዳማት ፡ በየትኛውም ፡ ዓለም ፡ ቢሆን ፡ የሚገ
ኙት ፡ ከተራራ ፤ ሰው ፡ ከራቀበት ፡ ብዙ፡ ችግር ፡ ካለበት፡
ከምድረ ፡ በዳ ፡ ውሃ ፡ ከሌለበት ፡ ዛፍ ፡ ከማይበቅልበት ፡
ብዙ ፡ ሥቃይ ፡ ካለበት ፡ እንዲሁም ፡ ከጫካው ፡ ውስጥ ፡
ብዙ ፡ አውሬዎች ፡ ካሉበት ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ፤ ይኸም ፡ አኳ
ኋን ፡ የቀደመውን ፡ የአተካከል ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ያስረዳ
ዳናል ፡ እንዲሁም ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ በምቹ ፡ ቦታዎች ፡
ይገኛሉ ፤ እነዚህም ፡ እንዲሁ ፡ የኋለኛውን ፡ የአተካከል ፡
ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሰፊው ፡ ያስረዱናል። ገዳማቱ፡ ሌላ፡ ልዩ፡
ዓለም ፡ በመሆናቸው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አጥፍቶ ፡ በመንግ
ሥት ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ ከገባ ፤ በዓለም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡
ሞተ ፡ ተቈጥሮ ፡ እንዲሁ ፡ መንግሥት ፡ በሰጠው ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ መሠረት ፡ ገዳሙ ፡ ተከብሮ ፡ አጥፊው ፡ አይነካም፡
ነበር ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ሥጋዊ ፡ ሥራ፡ ሲሠራ ፡ ወደ፡
ቀደመ ፡ ቦታ ፡ ሲመለስ ፡ በቀደመ ፡ ወንጀሉ ፡ ተይዞ ፡ ይፈ
ረድበት ፡ ነበር ።

<u>ገዳማቱ ፡ በ፪ ፡ ዓይነት ፡ ክፍል ፡ ይከፈላሉ</u> ፤
፩ኛው ፡ ክፍል ፡ የአንድነት ፡ ገዳም ፡ ይባላል ፤ ይኸም ፡
ማለት ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ የሆነው ፡ ሁሉ ፡ እንደየችሎ
ታው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ ይሥራ ፡ እንጂ ፤ የሚመገበው ፡
በአንድ ፡ ላይ ፡ ነበር ፤ የሁሉም ፡ ንብረቱ ፡ የሚቀመጥ ፡
በአንድ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ የተለየ ፡ ሀብት ፡ እንያዳንዱ ፡ ሳይ
ኖረው ፡ በኅብረት ፡ ሠርቶ ፡ በኅብረት ፡ አመስግኖ ፡ ስለ ፡
ሚኖር ፤ የአንድነት ፡ ገዳም ፡ ይባላል ።

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ፡ ክፍል፡ የሚገኙት ፡ መነኰሳት፡ በመምህሩና፡
በመጋቢው ፡ ፈቃድ ፡ ሲተዳደሩ ፤ ተልእኳቸውን ፡ ሲፈ
ጽሙ ፤ ችግራቸውን ፡ ሲያስወግዱ ፤ የሁሉ ፡ ኑሮ ፡ ዝግታ፡
ፀጥታ ፥ ሰላም ፡ የተሟላ ፡ ሆኖ ፡ ሕዝቡም ፡ በለጋስነት ፡
ሲረዳቸው ፡ ይገኛል ።

፪ኛው ፡ ክፍል ፡ ቊሪት ፡ ይባላል ። ይኸም ፡ ማለት ፡
እንደ ፡ ማንኛውም ፡ ገዳም ፡ ሆኖ ፡ መነኰሳቱ ፡ ብቻ ፡
እንደ ፡ ፈለጋቸው ፡ ሲወጡ ፥ ሲገቡ ፥ አንድ ፡ ጊዜም ፡
ሲበዙ ፥ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ሲያንሱ ፡ በግላቸው ፡ እየሠሩ ፡
የግል ፡ ጥሪት ፥ የግል ፡ ሀብት ፡ የሚያበጁና ፡ በዚ
ያም ፡ የሚተዳደሩበት ፡ ነው ። ራስ ፡ የመውደድና ፡ ልዩ ፡
ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ ለመኖር ፡ ይፈቅዳሉ ፡
ርዳታም ፡ ከሰው፡ ዘንድ ፡ ቢመጣ ፡ ተከፋፍለው ፡ ዕለቱን፡
የሚለያዩ ፡ ናቸው ፤ ሆኖም ፡ ይኸ ፡ እንደ ፡ ገዳም ፡ ሊቈ
ጠር ፡ የማይገባው ፡ ነው ፥ ምክንያቱም ፡ መነኰሳቱም ፡
ጥቂቶቹ፡ የደረጁት ፡ ሲቀመጡ፤ ሌሎች ፡ ግን ፡ እየጠሉት ፡
ስለሚሄዱ ፡ ገዳሙ ፡ ተራቊቶ ፡ ታሪኩ ፡ ጠፍቶ ፡ የሚገኝ
ብዙ ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ አለ ፡ ነው ።

እያንዳንዱ ፡ ገዳም ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ድርጅት ፥ ልዩ፡ ልዩ፡
አስተዳደር ፡ አለው ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፤ በመሠረቱ ፡ ውስ
ጣዊ ፡ አስተዳደሩ ፡ የሁሉም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

ም ክ ር ።

አንባቢ ፡ ሆይ ፤ ምንኵስና ፡ ከፍ ፡ ያለ፡ ማዕርግ ፡ ከባ
ድም ፡ ኑሮ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ተረዳህን ? ብዙዎች ፡ መመንኰስ ፡



ብቻ ፤ ወይም ፡ ምንኵስና ፡ ብቻ ፡ የሚያጸድቅ ፡ እየመሰላ
ቸው ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ ሄደው ፡ የሚመነኵሱ ፡ ወይም ፡
ቆብን ፡ በተላላኪ ፡ አምጥተው ፡ የሚደፉ ፡ አሉ ።

ይኸ ፡ ለመንኳሹም ፡ ለአመንኳሹም ፡ ሕገ ፡ ወጥ
ነት ፡ የኑሮ ፡ ሽፍትነት ፡ ነው ። ሁሉ ፡ በደንቡ ፡ ሲሆን ፡
መልክ፡ አለው ፡ በተለይም ፡ ምንኵስና፡ በደንቡ ፡ ሲሆን ፤
ከርሱ ፡ የበለጠ ፡ ሕይወት ፡ ከቶ ፡ የለም ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡
የበቁ ፡ በደንቡም ፡ የተጠበቁ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።

ገዳም ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ደረጃ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡
ማዕርግ ፡ ሲኖረው ፡ ለዚህ ፡ ብቻ ፡ የበቁ ፡ መግባት ፡ ሲገ
ባቸው ፡ የፈሪ ፡ ማንኳተቻ ፥ የሥራ ፡ ፈት ፡ መከማቻ ፡
ሁኖ ፡ ይገኛል ። አንተ ፡ መነኵሴ፡ ወገብህን ፡ በንጽሕና ፡
ዝናር ፡ ታጠቅ ፤ ክፉውን ፡ ከደግ ፡ ለይተህ ፡ ዕወቅ ፤ አባ፡
የተባለው ፡ ቅጽል፡ ከባድ ፡ ስለሆነ፡ ለሰነፎች፡ ወይም፡ ለደ
ካማዎች ፡ የሚሰጥ ፡ አይደለም ፥ ፍጹም ፡ አባት ፡ ይኸ ፡
ቀረህ ፡ የማይባል ፡ ማለት ፡ ነው ፥ ስለዚህ ፡ ለሁሉ ፡
ፍጹም ፡ አባት ፡ ኀያል ፡ መስተጋድል ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡
ገዳም ፡ ከመግባትህ ፡ በፊት ፡ ራስህን ፡ መርምር ፤ ማንኛ
ውንም ፡ የገዳም ፡ ወይም ፡ የምንኵስናን ፡ ሥርዐት ፤
ተማር ፤ ከሴት ፡ መራቅ ፥ ንጽሕናን ፡ መጠበቅ ፡ ጥቅሙ ፤
፩ኛ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ በምስጋና ፥ በቅዳሴ ፡ ለመ
ገናኘት ፡ ተገዥነትን ፡ ለመግለጥ ፡ ነው ፡ ከሁሉም ፡ በበ

www.ethiopianorthodox.org

ለጠ ፡ ለመሥራት ፡ እንዲመች ፡ ነው ። ፪ኛ ፤ የሕዝብ ፡ አገ ልጋይ ፡ ሁኖ ፡ ሕዝብን ፡ ለማስተማር ፤ የትሩፋት ፡ አብ ነት ፡ ሆኖ ፡ ለመታየት ፡ ለሕዝብ ፡ እውነተኛ ፡ ብርሃን ፡ የክርስቶስ ፡ ተከታይ ፡ ሆኖ ፡ ለመገኘት ፡ ነው ። አሁንም፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ለመሥራት ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይር ዳህ ፡ አሜን ።

# ማ ጠ ቃ ለ ያ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ሐሳብ ፡ አውጥቶ ፡ አውርዶ ፡ ጥቅሙንና ፡ ጉዳቱን ፡ ለይቶ ፡ ዐውቆ ፡ ሕይወቴን ፡ በንጽ ሕና ፡ በድንግልና ፡ አሳልፋለሁ ፡ ብሎ ፡ ከቈረጠ ፤ ድንግ ልናዊ ፡ ሕይወትን ፡ ገንዘብ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከሥጋዊ ፡ ፈቃድ ፡ ጋራ ፡ መዋጋት ፡ ንጽሕናን ፡ አጥብቆ ፡ መያዝ ፡ አለበት ። በንጽሕና ፡ የሚኖረውን ፡ ሰው ፡ የሚገ ጥሙት ፡ ፈተናዎች ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። ስማቸውና ፡ ዐይነታቸው ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ቈራጡ ፡ ድን ግል ፡ በቀላሉ ፡ ለሚያልፈው ፡ ነገር ፡ አለመታለል ፤ ለሥ ጋዊ ፡ ፈቃድም ፡ ተገዢ ፡ አለመሆን ፡ አለበት ። እንዲ ሁም ፡ በድንግልናዊ ፡ ሕይወት ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ በጥብ ቅና ፡ በቈራጥነት ፡ ለመሥራት ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ ለመሆንና ከብዙ ፡ ዓለማዊ ፡ ተግባር ፡ ለመራቅ ፡ ስለሆነ ፤ ሰዓት ፡ ሳይወስን ፡ መሥራት ፡ እንዳለበት ፡ ለማንቃትና ፡ ለማት ጋት ፡ ነው። ድንግሉም ፡ ዘወትር ፡ ሊሠራው ፡ የሚገባው፡ የክርስቶስ ፡ ስም ፡ የሚቀደስበትን ፡ መንግሥቱ ፡ የሚሰፋ በትን ፤ አምልኮቱ ፡ የሚጠናበትን ፤ እንዲሁም ፡ በጎ ፡ አድራጎትና ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ፡ የሚከናወንበትን ፡ መሆን፡ አለበት። እንዲሁም ፡ በየጊዜው፡ ሁሉ ፡ የሚሠራውን ፡ ስብ ከት ፡ መስበክ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንፈሳውያን ፡ መጻሕፍትን፡ ማወቅና ፡ መጻፍ ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

www.ethiopianorthodox.org

ድንግሉም ፡ ሰው ፡ ይኸን ፡ ቅዱስ ፡ ዓላማ ፡ ለመፈጸም ፡ እንዲሁም ፡ ድንግልናውን ፤ ንጽሕናውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ማንኛውንም ፡ መንፈሳዊ ፡ ተግባሩን ፡ በሚገባ ፡ ለማከናወን ፡ የጀመረውንም ፡ ሁሉ ፡ በትክክል ፡ ከግቡ ፡ ለማድረስ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ርዳታ ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ። ማለት፡ ሁል፡ ጊዜ፡ መጸለይ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ በጸሎት ፡ መነጋገር ፡ ይገባዋል ። ምክንያቱም ፡ ማንኛውም ፡ ሥራ ፡ በሰው ፡ ኀይል ፡ በሰው፡ ስሜት፡ ብቻ ፡ የሚጀመር ፡ የለምና ፡ ቢጀመርም ፡ ፍጻሜው ፡ አያምርም ። ስለዚህ ፡ በማንኛውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የግድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ርዳታ ፡ መጨመር ፡ አለበት ። ክርስቶስም ፡ ሲያስተምር ፡ ያለኔ፡ ምንም ፡ ልትሠሩ ፡ አትችሉም፡ ብሏልና፡ (ዮሐ፡፲፭፡ ፶)፡ ማንኛውም ፡ ተግባር ፡ ማንኛውም፡ የኑሮ ፡ ዘዴ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ስለዚህ፡ የጀመርኩትን ፡ አስፈጽመኝ ፤ የሠራሁትን፡ ሁሉ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቃድህ ፡ አድርግልኝ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መለመን ፡ ለማንኛውም ፡ ሰው ፡ የግድ ፡ ያስፈልጋል ።

ጋብቻን ፡ በመንቀፍ ፡ ወይም ፡ የራሱን ፡ ምኞት ፡ ብቻ፡ በመሻት ፡ ከጋብቻ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ቢርቅ፡ ወይም ፡ ቢንቅና ፡ ቢያቃልል ፡ ይበድላል ፤ ወንጀልም ፡ ይሠራል ፡



ማለት ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ የድንግልና ፡ ዋናው ፡ ዓላማ፡ መንፈሳዊ ፡ ተግባርን ፡ በጎ ፡ አድራጎትን ፡ ለመፈጸም ፤ ፀጋን ፡ ለመርዳት ፤ ወንጌልን ፡ ለማስተማር ፡ እንጂ ፡ ሥን፡ ፍጥረትን ፡ በመንቀፍ ፡ አይደለምና ፤ በዚሁ ፡ ዓላማ ፡ ቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡ እንዲሁም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባቶች ፡ ሁሉ ፡ በድንግልና ፡ በንጽሕና፡ ኑረዋል ። ብዙዎች፡ ደናግል ፡ ወንዶችም ፡ ሴቶችም ፡ ይኸን ፡ ዓላማ ፡ በመከተል ፡ ዕድሜ ፡ ልካቸውን ፡ ሙሉ ፡ ብዙ ፡ ግዳጅ ፡ ፈጽመዋል ። ብዙ ፡ ድርጅትን፡ አቋቁመዋል ። ድንግልናዊ፡ ሕይወት ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ቅዱስም ፡ ሕይወት ፡ ነው ፡ ስንል፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በዘረዘርነው ፡ ዓላማ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ነው ። ይኸንም ፡ በሚገባ ፡ ለመፈጸም ፡ ልዑል ፡ አምላክ ፡ ይርዳን ። የጀመርነውን ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ያስፈጽመን ። በየጀመርነው ፡ ጸንተን ፡ ከእውነተኛው ፡ አምላክ ፡ ዋጋችን፡ ለማግኘት ፡ ያብቃን ።

አሜን ።

0911860113
0111271609
D.N. Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org